ማውጫ

መግቢያ 4

ክፍል አንድ 5

1. አጠቃላይ ሁኔታ 5

1.1. ዓላማ 5

1.2. ውጤት 5

1.3. ወሰን 6

1.4. የሥልጠናው ተሳታፊዎች 6

1.5. ሥልጠናው የሚወሰደውጊዜ 6

1.6. ትርጓሜ 6

1.7. ታክስ የመጣልና የማስከፈል ሥልጣን 7

1.8. ታክስ ለማስከፈል የህጉ ተፈጻሚነት ወሰን 7

1.8.1. ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ሰው፣ 8

ክፍልሁለት 9

2. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር (ሠንጠረዥ "ለ") 9

2.1. ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ 9

2.3. ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች 9

2.3.1. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ 9

2.3.2. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ግብር 10

2.4. የኪራይ ቤት፣የቤት ዕቃና መሣሪያ የእርጅና ቅናሽ 10

2.5. የኪራይ ገቢግብር ማስከፈያ መጣኔ 11

2.6. የተከራይ አከራዮች 12

ክፍል ሦስት 16

3. የንግድ ስራ ገቢ ግብር (ሰንጠረዥ ሐ) 3.1. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ 16

3..1. የንግድ ስራ ገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ 17

3..1. በታክስ ህጉ የተፈቀዱ ሌሎች ዝርዝር ተቀናሽ ወጪዎች 18

3.3.1.1. ውጭ ሃገር የሚገኝ የዋናው መስሪያ ቤት ወጪ 20

3.3.1.2. የወለድ ወጪ 20

3.3.1.3. ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተደረገ ስጦታ፣ 21

3.3.1.4. በታክስ ህጉ የተፈቀዱ የእርጅና ቅናሽ አሠራር 21

3.3.1.5. የእርጅና ቅናሽ ስሌት ዘዴዎች 23

3.3.1.6. ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ 23

3.3.1.7. ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ 24

3.3.1.8. የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች 24

3..2. ጥገናዎችና ማሻሻያዎች ላይ የሚደረግ የወጪ ተቀናሽ....26
3.3. የማስታወቂያ ወጪ....27
3.4. በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት የሚያጋጥምን ብክነ ትእንደወጪ ስለመያዝ....28
3.5. ተቀናሽ የሚደረግ የመዝናኛ ወጪ....28
3..6. የማይሰበሰብ ዕዳ....29
3.7. ኪሳራ....29
3.8. ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች ኪሣራ መጠባበቂያ....30
3..9. የህይወት መድን ንግድ ሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ....31
የመከራ ጥያቄ ሦስት....32
ክፍል አራት....33
4. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ ዓመት....33
4.1. የሂሳብ አያያዝ ዘይን ስለመለወጥ....33
4.2. የካፒታል ሀብት ሲተላለፍ የሚያዝ መረጃ....34
4.4. የሒሳብ መግለጫ ይዘቶች....36
4.5. መረጃ እንዲቀርብ ስለሚሰጥ ማስታወቂያ....37
4.6. የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ግብር ከፋዩ ሶፍትዌር የሚጠቀም ከሆነ....37
4.7. ሂሳብ መዝገብ ባለመያዝ ከሚጣል መቀጫ ነጻ ስለመሆን/አለመሆን....37
4.8. የግብር ከፋዩ ወጪተቀባይነት ስያጣ ማስተካኪያዎች....38
4.9. ሰነድ በሚመለከተው አካል ስለማስመዘገብ....38
4.10. የሂሳብ መዝገብ አዘገጃጀት....39
4.11. ግብር ከፋዩ ያቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችሉ ምክንያቶች....41
4.12. ስህተቶችን ስለማረም....42
4.13. በማስታወቂያ መረጃ ወይም ማስረጃ መጠየቅ....43
4.14. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን....43
4.15. ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች....44
ክፍል አምስት....45
5. ድርጅትን በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥና የኩባንያ እንደገና መደራጀት....45
5.1. አንድን ድርጅት በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥ (34)....45
5.2. የኩባንያ እንደገና መደራጀት....45
5.3. የማዕድንና የነዳጅ ስራዎች ገቢ ግብር....46
5.3.1. የማዕድንና የነዳጅ ስራዎች ልዩ ባህሪ....46
5.3.2. ፈቃድ በተሰጠው ሰውና በስራ ተቋራጭ ላይ ግብር ስለመጣል....47
5.3.3. በማዕድን ወይም በነዳጅ ስራዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎችን ስለመገደብ....47
5.3.4. የማዕድን ወይም የነዳጅ መብት ስለማስተላለፍ....50
5.3.5. የማዕድን ወይም የነዳጅ መብትን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለማስተላለፍ....50

5.4. ዓለም አቀፍ ግብር.....51
5.4.1. በውጭ አገር የተከፈለን የንግድ ስራ ገቢ ስለማካካስ.....51
5.4.2. የውጭ አገር የንግድ ስራ ኪሳራዎች.....52
5.4.3. ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር (Thin capitalization).....52
5.4.4. ግብርን በሚመለከት የሚደረጉ ስምምነቶች (tax treaties).....54
5.5.1. ከግብር ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ስለመከላከል.....59
5.5.2. የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ.....61
ማጠቃለያ.....62
ማጣቀሻ (Referance).....63

መግቢያ

የታክስና ቀረጥ ስርዓት የህዝብና የመንግስት ግንኙነት ከሚገለጽባቸው አበይት መንገዶች መካከል አንዱ ሲሆን ሥርዓቱም መንግስት በሰው ልጅ ኑሮ ውስጥ ገዥ ስርዓት ሆኖ በተገለጸበት ዘመን እንደተጀመረ ይነገራል፣ምክንያቱም መንግስት ለሚያከናውናቸው ተግባራትም ሆነ ለሚያስተዳድረው ህብረተሰብ ለሚያቀርባቸው ኢኮኖሚያዊም ሆነ የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦቶች ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ ያስፈልገዋል፣የዚህ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ ደግሞ በዋነኝት የሚገኘው ከሰዎችና ድርጅቶች የሚሰበሰብ የግብር/ታክስ ገቢ ነው፣ስለሆነም የአንድን አገር የመንግስት ሥርዓት ከግብር/ታክስ ሥርዓት ለይቶ ማየት የሚታሰብ አይሆንም።

የግብር/ታክስ ሥርዓት ከገቢ ምንጭነት በተጨማሪ በህብረተሰቡ ዘንድ የሀብት ክፍፍል ለማድረግ፤ የሀገርን የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫ ለመምራት፤ ኢንቨስትመንትን ለማነቃቃት እና ዕድገትና ልማትን ለማፋጠን የሚያገለግል የፊስካል ፖሊሲ መሣሪያ ነው፤በመሆኑም

በማናቸውም የዘመናዊ ግብር/ታክስ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ የግብር፣ ታክስና ቀረጥ ሥርዓት በግልጽ በህግ መመራት ይጠበቅበታል፣ይህም የግብር/ታክሱ ግዴታ በግብር ከፋዩ ዘንድ ተቀባይነትና ተፈፃሚነት እንዲኖረው ሕጋዊ መሠረትን ስለሚያደርግ ነው፣በመሆኑም ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የግብር/ታክስ ሥርዓት ተፈጻሚ የሚደረግ የታክስ ህግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታን ያገናዘበ እንዲሆን በየጊዜው እየተፈተሸ ማሻሻያ የሚደረግበት ይሆናል።

በዚህም መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ/ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2 ዐ0 8 በስራ ላይ እንዲውል ተደርጎል።

የገቢ ግብር አዋጁ የአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃ ጋር የተጣጣመ እና የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያግዝ ዘመናዊና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት ለመዘርጋት እና የግብር አከፋፈሉ ሥርዓት ፍትሀዊነት ያለውና ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች በግብር መረብ ውስጥ ለማስገባት የተቀረጸ ነው።

ክፍል አንድ

1. አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

- ዋና ዓላማ፤
- **ከሥልጠናው በኋላ ሠልጣኞች፤**

- የገቢ ግብር የሚከፈልባቸውን የሰንጠረዥ "ለ" የኪራይ ገቢ ግብር እና የሰንጠረዥ "ሐ" የንግድ ሥራ ገቢ ግብሮች በታክስ ሕግ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ግብራቸውን አሳውቀው መክፈል እንዳለባቸው በሥልጠና ላይ በሚደረግ ውይይት ይረዳሉ።
  - ዝርዝር ዓላማ፤
- በሞጁሉ ሥልጠና ሂደት ሠልጣኞች:-
  - ✓ የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎችን በማስላት ያሳያሉ፤
  - ✓ በገቢ ግብር አዋጅ የተካተቱትን የሰንጠረዥ "ለ" ገቢዎችን ምንነት ይገልጻሉ
  - ✓ **የዕርጅና ቅናሽ ዘዴዎችን እና ስሌቶችን በምሳሌ ያስረዳሉ**

- ✓ የማይሰበሰብ እዳ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ምን፤ምን መስፈርቶች ሲሟሉ እንደሆነ ያብራራሉ
- ✓ በአንድ የግር ዘመን ኪሳራ የገጠመው ሰው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው ለስንት አመታት እንደሆነ ይገልጻሉ
- ✓ ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ ግብር ከፋዩ ኪሳራ ቢያጋጥመውኪሳራውን እንዴት እንደሚያሸጋግር ያብራራሉ
- ✓ የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዴት እንደሚወሰን ያስረዳሉ
- ✓ ከግብር መሸሽ (tax avoidance) እና ግብር መሰወር (tax evasion) መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራሉ

1.2. ውጤት

- ✓ በሰንጠረዥ "ለ" እና በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት የገቢ ግብር የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች በአዋጁ፣ በደንቡ እና በመመሪያው ላይ የተደነገጉትን አጠቃላይ የህ እውቀት ይኖራቸዋል፤
- ✓ የገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን ግልጽ በማድረግ ለመልካም አስተዳደር ችግሮች መንስኤ በሚሆኑ የሕግና የአፈጻጸም ብዥታዎች ላይ መግባባት ይደረሳል፤
- ✓ የገቢ ግብር የሚከፈልባቸውን የሰንጠረዥ "ለ" የኪራይ ገቢ ግብር እና የሰንጠረዥ "ሐ" የንገድ ስራ ገቢ ግብሮች አውቀው በታክስ ሕግ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ግብራቸውን አሳውቀው ይከፍላሉ ።

1.3. ወሰን

የማሠልጠኛ ሰነድ ሽፋን

- ✓ ለሰንጠረዥ "ለ" አጠቃላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በደንብ ቁጥር 410/2009 የተደነገጉትን የሚያካትት ሲሆን ፣
- ✓ ለሰንጠረዥ "ሐ" በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በደንብ ቁጥር 410/2009 እንዲሁም እነዚህን አዋጅና ደንቦች ተከትለው የወጡ ስለተቀናሽ ወጪዎች መመሪያ ቁ 5/2011፣ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 176/ 2014፣ መመሪያ ቁጥር 146/2011 የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ፤የግምት ታክስ ስሌት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 138/2011፣ መመሪያ ቁጥር 8/2011 የካፒታል ሃብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር እና አጠቃላይ በአዋጁ ያሉትን የወል ድንጋጌዎች እና የማዕድን እና የነዳጅ ሥራዎችን ፣አለማቀፍ የገቢ ግብር እና የግብር ስምምነት (Double tax Treaty) የሚያካትት ነው።

1.4. የሥልጠናው ተሳታፊዎች

ሥልጠናው በግብር ከፋይነት የተመዘገቡትን ድርጅቶች በዘርፋቸው በመለየት የሚሰጥ ሲሆን የኩባንያ፣የሼርካምፓኒ፤ኃ.የተ.የግ.ማ(PLC)፤የዕሽሙር ማህበር(Jointventure)፤የሚመለከተው ሠራተኛ በዋንኝነት የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሠራተኞች ወይም ሥራ አስኪያጅ፣ እና ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚሠለጥኑ ይሆናል።

1.5. ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ

- ➢ ይህን ሥልጠና ለማሠልጠን 18 ሰዓት ይጠይቃል።

1.6. ትርጓሜ

- ✓ **ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ ማለት፡- በግብር ዓመቱ ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው።**
- ✓ **የንግድ ስራ ማለት፡- በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣የንግድ፣የሙያ፣ወይም ቬንቸሸናል ስራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠው አገልግሎትቤት ማራየትን አይጨምርም፣በንግድ ህግ መሰረት የንግድ ስራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማንኛውም ስራ፣ ሀንጻ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው አላማ ምንም ቢሆን ማንኛውንም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃ.የተ.የግ.ማህበር የሚሰራው ማንኛውም ስራ፤**
- ✓ **የንግድ ስራ ሃብት ማለት፡-የንግድ ስራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ስራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፤**
- ✓ **ራሱን የቻለ ስራ ተቋራጭማለት፡-ስራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራት እና የመቆጣጠር በቂ ስልጣን በሚሰጠው ውል መሰረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤**
- ✓ **የቴክኒክ ክፍያ ማለት፡-ለቴክኒካዊ፣ሙያዊ፣ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ነው፤**
- ✓ **የንግድ እቃ ማለት፡-ማንኛውም የተመረተ፣የተፈበረከ፣የተገዛ፣ወይም ለማምረት፣ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፤ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ ወይም ለጭነት ወይም ለስራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ፤**
- ✓ *ሌሎች ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላትና ሀረጎች* በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በደንብ ቁጥር 410/2009 እንዲሁም እነዚህን አዋጅና ደንቦች ተከትለው በወጡ *መመሪያዎች* ላይ የተሰጠ ትርጉም *ይይዛሉ።*

1.7. ታክስ የመጣልና የማስከፈል ሥልጣን

- ➢ ከታክስ የሚሰበሰብ ገቢ ለአንድ *መንግስት* ህልውና እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ ታክስ የመጣልና የማስከፈል *ሥልጣን* ለመንግስት ብቻ የተሰጠ *ሥልጣን* ነው።ለግለሰብ ወይም ለሌላ አካል የዚህ ዓይነት *ሥልጣን* በየትኛውም ዓለም አይሰጥም። ታክስን በተመለከተ የፌዴራል *መንግስት* ያለውን ስልጣን በ ህገ-*መንግስቱ* ከአንቀጽ 96 እስከ አንቀጽ 99 በዝርዝር ተቀምጧል።
- ➢ የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ለፌዴራል *መንግስት* በህገ *መንግስቱ* በተሰጠው ታክስና ግብር የመጣልና የማስከፈል *ሥልጣን* መሠረት በሁለት *መሠረታዊ* የታክስ አጣጣል *መሠረቶች* (ወሰኖች) የታክስ ህግ ድንጋጌዎችን የሚያስቀምጥ ሲሆን እነዚህም፤

ሀ. ነዋሪነትን *መሠረት* ማድረግ፣

ለ. የገቢ ምንጭን *መሠረት* ማድረግ ናቸው።

1.8. ታክስ ለማስከፈል የሀገ ተፈጻሚነት ወሰን

- ➢ የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በዓለም ዙሪያ በሚያገኙት ገቢ እንዲሁም
- ➢ ኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የኢትዮጵያ ምንጭ በሆነ ገቢ ላይ ግብር የሚጣልባቸው ሲሆን ፣እከፋፈሉን፣አወሳሰኑንና አሰባሰቡም ተፈጻሚ ይደረጋል።

ሀ. ነዋሪነት

- ➢ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ

- ✓ ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ (domicile) ያለው፣
- ✓ በመንግስት ተመድቦ በውጭ አገር የሚሠራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ 91 ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ፣

➢ **ነዋሪ የሆነ ድርጅት**

- ✓ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ /የተመሠረተ/፣
- ✓ ወሳኝ የሆነ የሥራ አመራር የሚሰጥበት ሥፍራ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው፣

ለ. የገቢ ምንጭ

- ➢ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ ሥራ ገቢ
- ➢ ነዋሪ የሆነ ሰው በውጭ አገር ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅቱ አማካኝነት ከውጭ አገር የሚያገኘው ገቢ ከውጭ ምንጭ የተገኘ ገቢ ነው

1.8.1. ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ሰው፣

- ➢ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣
- ➢ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅቱ ከሚያስተላልፋቸው ዕቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ ዕቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በቀጥታ በማስተላለፍ የሚያገኘው ገቢ፣
- ➢ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ማናቸውም የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ ሌሎች የንግድ ሥራዎች፤

ክፍልሁለት

2. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር (ሠንጠረዠ “ለ“)

2.1. ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ

አከራይ ወይም የተከራይ አከራይ ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፈን የቤት ኪራይ ገቢ የተቀበለ እንደሆነ አከራዩ ወይም የተከራይ አከራዩ በዚህ ዓይነት የተቀበለው ጠቅላላ የቤት ኪራይ ገቢ መጠን፣ገቢውን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ተደርጎ ይቆጠራል፤ሆኖም በዚህ የገቢ መጠን ላይ የሚከፈለው ግብር የቤት ኪራይ ገቢው ለሚሸፍነው የግብር ዓመታት በማከፋፈል ይሰላል።

2.2. ቤት በማከራየት የሚገኝ ጠቅላላ ገቢ የሚጨምራቸው ገቢዎች

- የኪራይ ዋጋ ቁጣሪን ወይም ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ በኪራይ ወሉ መሠረት ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የሚያገኘው ማናቸውም የገንዘብ መጠን፣
- በኪራይ ውሉ መሠረት ተከራይ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎች የሚከፍላቸው ክፍያዎች፣
- በቤቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ ግብር ከፋዩ የያዘውና በግብር ዓመቱ ያልተጠቀመበት ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማናቸውም ቦንድ፣ዋስትና ወይም ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን፣
- ለግብር ከፋዩ ከሚከፈለው ኪራይ በተጨማሪ በኪራይ ውል መሠረት ተከራይ ራሱ ለቤቱ እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚያወጣው ገንዘብ፣
- ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል።

2.3.ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

2.3.1. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ

- በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ ይያዛሉ።
    - ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኝ ግብር ከፋዩ ለመንግስት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፣

2.3.2. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ

- ገቢውን ለማግኘት የወጣና በግብር ከፋዩ የተከፈለ አስፈላጊ የሆኑ (ገቢውን ለማግኘት፣ ዋስትና ለመስጠት እና ሥራውን ለማሰቀጠል ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፤
- ቤቱ ያረፈበት የመሬት ኪራይ ፣የጥገና ወጪ፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና የመድን አርቦን፣ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኝ ግብር ከፋዩ ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች ፣
- በነባ ወይም በኪራይ የያዘው ቤት ስም የሚከፈል የውሃ፣ የስልክ፣የመብራት ወጪዎች በውሉ ተከራይ እንዲከፍሉ ከተገለፀ ወጪው ስለማውጣቱ ደረሰኝ ካቀረበ ይያዝለታል
- የኪራይ ቤቱ እና የመኖሪያው ቤት በአንድ የመብራት፣ የስልክ፣ የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀሙ ከሆነ ለነዚህ የወጣው ወጪ 75 በመቶ በወጪነት ተቀናሽ ሊያዝ ይችላል።
- በብድር ለተገኘ ወለድ ክፍያ በወጪነት የሚያዘው ለኪራይ አገልግሎት ብቻ መጠን ልክ ነው፤
- ለኪራይ የሚያስገኝባው ህንጻ ብድር የተወሰደ ከሆነ እና የብድር ወለድ ወጪ የሚያዘው፡-
    - ህንፃው እሰከሚገባ ድረስ ያለው የህንፃው ዋጋ ሆኖ በእርጅና ቅናሽ የሚታሰብ ሲሆን፤
    - ህንፃው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኃላ በወጪነት የሚፈቀድ ይሆናል፤
- ኪራይ አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ የሚወጣ ወጪ የሚያዘው፡-
    - በተለያየ ዝግጅት ላይ ለሚደረግ የማስታወቅ ስራ ሲሆን ከጠቅላላው ኪራይ ገቢ 3 በመቶ ባልበለጠ፣
    - ለመገናኛ ብዙሃን ወይም ለማስታወቂያ ድረጅት ከሆነ በሙሉ ተቀናሽ ይሆናል፤
- ለኪራይ የተገኘባው ህንፃ ለሌላ ዓላማ ዕስካልዋለ ድረስ ግብር ከፋዩ ህንፃውን ለኪራይ አገልግሎት ዝግጁ ያደረገ ከሆነ ህንፃው ባይከራይም ለኪራይ እንደዋለ ተቆጥሮ እርጅና ቅናሹ እንደ ወጪ ይያዛል፤

2.4. የኪራይ ቤት፣የቤትዕቃና መሣሪያ የእርጅና ቅናሽ

- አንድ ህንፃለኪራይ አገልግሎት እና ለሌላ ገቢ ለማስገኘት የዋለ እንደሆነ የወጪው ክፍፍል ጥቅም ላይ በዋለበትና በገቢው ድርሻ ልክ ነው፤
- አንድ እቃ ወይም ማሽን የዕርጅና ቅናሽ ሊያገኝ የሚችለው በአመቱ ውስጥ የንግድ ስራ ገቢውን ለማግኘት አገልግሎት ለሰጠበት ጊዜ ብቻ ይሆናል

  ለምሳሌ፡-መጋዘኑን ከቡና መፈልፈያ ማሽኑ ጋር የተከራየ ግብር ከፋይ የማሽኑ ዋጋ 40 ሺ ብር ቢሆን እና ማሽኑ ለንግድ ስራ ገቢው አገልግሎት የሰጠው ከየካቲት አንድ እስከ ሰኔ 30 ብቻ ቢሆን እና ማሽኑ በአመት 20 በመቶ ዋጋው እየቀነሰ ቢሄድ፤ በቀጥተኛ የዕርጅና ቅናሽ ዘዴ ቢሰላ፤

  5 ወር ሲባዛ በ 30 ቀናት = 150 ቀናት ለንግድ ስራው አገልግሎት የሰጠበት ቀን፤

  ((40,000 x 20/100) x 150/365) 3,333 ብር ይሆናል ከየካቲት አንድ እስከ ሰኔ 30 ያለው የማሽኑ የዕርጅና ቅናሽ፤

  የማሽኑ የአገልግት ዘመን 5 አመት ቢሆን እና ለቀጣዮቹ አራት አመታት ሙሉ አገልግሎት ቢሰጥ ማሽኑ 40,000 x 20/100 = 8,000 ብር ዋጋው እየቀነሰ ይሄዳል:: ከፊል አገልግሎት ለሰጠበት ለመጀመሪያው አመት ግን በ 3,333 ብር ዋጋው ይቀንሳል ማለት ነው።
- አንድ ህንጻ ለሌላ አገልግሎት ከዋለ የእርጅና ቅናሹ ወጪው ተለይቶ መቅረብ አለበት፤ ተለይቶ ካልቀረበ ከጠቅላላው የህንፃ ዋጋ ለኪራይ አገልግሎት የዋለውን ስፋት መጠን በማስላት ተቀናሽ ይደረጋል፤
- ለእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሠረት ሚሆነው ዋጋ፡-
  - ለኪራይ የዋለው ህንፃ የተሰራበት ወይም የተገዛበት ዋጋ ነው ወይም
  - ይህ ካልቀረበ ህንፃው የተሰራበት/የተገዛበት የገበያ ዋጋ 70 በመቶ በመያዝ የዕርጅና ቅናሽ ይሰላል፤
  - በባል ወይም በሚስት ለተመዘገበ ህንፃ ህንፃው ለኪራይ አገልግሎት እንዲውል፣ተቀናሽ እንዲጠየቀበትና ህንፃው ሲሸጥ ተገቢው ግብርና ታክስ እንዲከፈልበት የባልና ሚስት ስምምነት ሰነድ፤ የኪራይ ቤቱ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ሆኖ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መዋቅራዊ ማሻሻያ የተደረገ መሆኑን፣
  - ከቤቱ ጋር የተከራየ ማንኛውም የቤት ዕቃ እና መሣሪያ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት መሆኑን።
- ለእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሠረት ሚሆነው የተገዛበት /የተሰራበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ በግብዓትነት የተካካሰለት ከሆነ በተካካሰው መጠን ልክ ከእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው ዋጋ ውስጥ መቀነስ አለበት፤
- በታክስ ከፋዩ ስም ላልተመዘገቡ ሀብቶች የእርጅና ተቀናሽ ወጪ አይፈቀድም፤የሚፈቀደው ስልጣን በተሰጠው አካል ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው።

2.5. የኪራይ ገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ

- በድርጅቶች የሚከፈለው የኪራይገቢግብርመጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ)ነው።
- የግለሰቦችየኪራይገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔዎችየሚከተሉትናቸው።

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት	የኪራይ ገቢግብር መጣኔ	ተቀናሽ
0-24,000	0%	0
24,001-48000	15%	3,600
48,001-84,000	20%	6,000
84,001-120,000	25%	10,200
120,001-168,000	30%	16,200
ከ 168,000 በላይ	35%	24,600

- ይህ ሠንጠረዥ አልፎ አልፎ ከሚከራዩ ንብረቶች በሚገኘው ገቢ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ፡

2.6. የተከራይ አከራዮች

- የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው።
- ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።

2.7. ከውጭ ሀገር የቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

- በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በውጭ አገር ባገኘው የኪራይ ገቢ ግብር ይከፍላል።
- የተጣራ የውጭ አገር ኪራይ ገቢ ማለት ከተገኘው ኪራይ ጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ ወጪዎች ከተቀነሱበኃላያለውነው፤
- በውጭ አገር የተከፈለ ግብር ማካካሻ መብት አለው፤

➢ ሊካካስ የሚችለው:-

- ✓ ገቢው ከተገኘ እለት በአሉት ሁለት ዓመታት በኋላ የከፈለ እንደሆነና፤
- ✓ በውጭ አገር የተከፈለበትን ደረሰኝ ሲያቀርብ ነው፤(በአዋጁ 979/2008 አ-45(3))

➢ ከዚህ ጋር ተያይዞ፡-

ሀ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪን በሚመለከት ከቤት ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔ ማለት:-

- ✓ ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በግብር ዓመቱ ነዋሪው ግብር በሚከፍልበት ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቤት ኪራይ ገቢግብር መቶኛ ነው።

ለ) የውጭ ሀገር ገቢ ግብር ማለት:-

- ✓ በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር የክልል መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ቅጣትን፣ተጨማሪ ግብርን ወይም ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም።

ሐ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪ ግብር ከፋይን በሚመለከት የተጣራ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢማለት፡-

- ✓ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ገቢውንከማግኘት ጋር በተገናኘ የተፈቀዱ ተቀናሽ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው።

2.8. የቤት ኪራይ ኪሣራዎች

- ❑ የተፈቀደለት ተቀናሽ ወጪ ከግብር ኣመቱ ጠቅላላ ቤት ኪራይ ገቢ በበለጠው ልክ በግብር ዓመቱ እንደደረሰ ኪሳራ ይቆጠራል፤
- ❑ አንድ ቤት አከራይ ለአንድ የግብር አመት የደረሰበትን ኪሳራ ኪሳራው ተካክሶ እስከሚያቅ ድረስ ለ 5 አመታት ኪሳራውን ማሸጋገር ይችላል ነገርግን አንድ አከራይ በግብር ከፋይነት ዘመኑ ኪሳራን ማሸጋገር የሚችለው ሁለት ጊዜ ብቻ ይሆናል።
- ❑ ለንግድ ስራ ገቢ ግብር ኪሳራን ስለማሸጋገር በአዋጁና በደንቡ የተቀመጡ ድንጋጌዎች የቤት ኪራይ ኪሣራ ለደረሰበት ግብር ከፋይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2.9. የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ

- ❑ ለኪራይ የሚሰራው ቤት እንደተጠናቀቀ ወይም ተከራይቶ ከሆነ ስራ ተቋራጩ እና የቤቱ ባለቤት ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣አድራሻና የከራይ ታክስ የሚከፍልበት መለያ ቁጥር ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የአካባቢ አስተዳደር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።
- ❑ የቀበሌ አስተዳደሩ ወይም የአካባቢ አስተዳደሩ ከስራ ተቋራጩና ከቤቱ ባለቤት ያገኙት መረጃ ለግብር ባለሥልጣኑ መግለጽ አለባቸው።

2.10. የኪራይ ገቢ ግምት አወሳሰን

የሂሳብ መዝገብ መያዝ ሲገባው በአግባቡ ያልያዘ አከራይ ወይም የተከራይ አከራይ የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩን የኪራይ ገቢ ግብርን በግምት የመወሰን ስልጣን አለው

- ❑ **የኪራይ ገቢ ግብር በግምት የሚወሰነው የሚከተሉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግነው**
  - ➢ ውልንመሰረትበማድረግ፣
  - ➢ 3 ኛወገን መረጃ እና የተሻለው ተወስዶ፣
  - ➢ ወቅታዊ መራጃ፤ የአካባቢን መረጃ፣በአካል የገበያን ሁኔታ በማጥናት፣
    - ✓ በግምቱ መሰረት የተደረሰበት ገቢ ለተ.እ.ታ. (VAT) መሰረትሊወሰድይችላል፣
  - ➢ ለደረጃ**“ሀ”** እና**“ለ”**በግምት ግብር አወሳሰን የጠቅላለው ኪራይ ገቢ 35% እንደ ወጪ ተይዞ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ መሰረት ይሆናል፣

የመከራ ጥያቄ አንድ

1. የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔዎችን በማስላት ያሳዩ፤

ሀ. ጂ.ኤም ኃ.የተ.የግ.ማህበር ድርጅት ስም የተመዘገበውን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ባለ 5 ፎቅ የሆነውን ህንፃ የ 4 ቱን ፎቅ 20 ክፍሎች ለትምህርት ቤት አገልግሎት ለወ/ሮ መና ወረደ ለአንድ ዓመት የሚቆይ በየወሩ ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ለማከራት ይስማማል። አምስተኛውን ፎቅ ግን ሳይከራይ ተቀምጧል። ወ/ሮ መና ከሐምሌ 1 ጀምሮ የሚቆጠር በሰኔ 30 የሚጠናቀቅ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ውል በየወሩ ብር 45,000 (አርባ አመስት ሺህ) ለመክፈል ለአንድ ዓመት የሚቆይ ውል የገባች በመሆኑ የአስራ ሁለት ወር ክፍያ ከፍላለች።ድርጅቱ 50,000 (ሃምሳ ሺህ) የመማሪያ ወንበሮች ለመግዛት 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) የመማሪያ ሰሌዳዎችን በየክፍሉ ለማሟላት እና በተጨማሪም ህንፃውን ማደሻ 30,000(ሠላሳ ሺህ) ወጪ አውጥቷል ከዚህ ውስጥ ግን 7,000 ብር አምስተኛውን ፎቅ ለማደስ የወጣ ነው። ነግርግን ድርጅቱ ያወጣው ወጪ በታክስ ኦዲት ተቀባይነት ስላጣ የታክስ ስሌቱ በግምት ሲወሰን፡-

- ጥያቄ

ሀ. የአከራዩ ዓመታዊ ገቢ ስንት ነው?

ለ. ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ምን ያህል ነው?

ሐ. አከራይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ አለበት ወይስ የለበትም?

መልስ

ሀ.ዓመታዊ ገቢው 45,000 x 12 = 540,000

ለ.ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ከጠቅላላ ገቢው 65 % ነው ⁚ ስለዚህ 540,000 x 65% = 351,000 ታክስ

የሚከፈልበት ገቢ ነው ⁚ ግብር 351,000 × 0.3 =105,300

ሐ..አከራዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፍላል⁚ 540,000 × 0.15 = 81,000

ለ. ዋይ.ኤም ኃ.የተ.የግ.ማ አንድ የንግድ ማእከል ተከራይቶ የሚያከራይ ሲሆን ከሚያከራየው አጠቃላይ የአመት ገቢው 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ብር ነው። ለአንድ ዓመት ለዋና አከራዩ የሚከፍለው 300,000 (ሶስት መቶ ሺ) ብር ነው። አከራዩ ገቢውን ለማግኘት ቤቱን ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ለፖርቲሽን 20,000 ደግሞ ለማስዋቢያ አውጥቷል።

- ጥያቄ፡-

1. ግብር የሚከፈልበት ገቢ አስሉ

መልስ፡-

ሀ. የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ የተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ)

ለ. ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ ብር 300,000 (ሶስት መቶ ሺህ)

ሐ. ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች ወጪዎች ብር 70,000 (ሰባ ሺህ)

መ. መከፈል ያለበት ታክስ 500,000- (300,000+50,000+20,000) = ግብር የሚከፈልበት የተከራይ አከራይ ገቢ 130,000 ታክስ=130,000 x 30 % 39,000=

የሙከራ ጥያቄ ሁለት

1. በገቢ ግብር አዋጅ የተካተቱትን የሰንጠረዥ "ለ"ገቢዎችን ምንነት ግለጹ

ክፍል ሦስት

2. የንግድ ስራ ገቢ ግብር (ሰንጠረዥ ሐ)

3.1. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ

- ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ የሚባለው በግብር ዓመቱ ከተገኘው ጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ በህግ የተፈቀዱ ወጪዎች ተቀንሰው የሚገኘው የተጣራ የገቢ መጠን ነው።
- ግብር የሚከፍልበት የንግድ ስራ ገቢ የሚወሰነው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች (IFRS) መሠረት በሚዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም የገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል።
  - ሆኖም ግን ፦-
  - የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ፣
  - የገቢ ግብር ደንብ፣ እና
  - የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣቸው መመሪያዎች እንደተጠበቁ ይሆናሉ።

የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የኦዲት ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ አጠቃላይ ተቀባይነት ያለውን የሒሳብ አያያዝ መርህ (Generally Accepted Accounting Principles) መሠረት በማድረግ የሂሳብ መዝገቡን ማዘጋጀት አለበት።

የንግድ ስራ ገቢ

- የንግድ ስራ ገቢ የሚበለው ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን በማስተላለፍ እና አገልግሎቶችን በመስጠት(መቀጠርን ሳይጨምር) የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ስራ ያገኘው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፣
- የንግድ ስራ ሃብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን ፣
- የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርገው የተወሰዱ ሌሎች ማናቸውም ገቢዎች፣

- የካፒታል ንብረት የሆነን የንግድ ስራ ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከተሉት ሁለት የግብር አይነቶች ሊወሰኑ ይችላሉ።
    - የንግድ ትርፍ ግብር (30 በመቶ)
    - የካፒታል ዋጋ ዕድገት ግብር (15 በመቶ)
- ለንግድ ስራው ሃብት የተደረገው ወጪ ከንግድ ስራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን በንግድ ስራ ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን ከወጪው በላይ የሚገኘው ጥቅም ደግሞ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ግብር ይከፈልበታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በምሳሌ ለማየት ያህል፦

  ምሳሌ፦**-1** ኤክስ.ዋይ.ዜድ የሚባል ኩባንያ አንድ ኮምፒተር 100,000 ብር ገዝቶ 75,000 ብር ሸጠው። ኮምፒተሩ 50,000 ብር የእርጅና ቅናሽ ተደርጎለታል።

  100,000 - 50,000 = 50,000 ብር ይሆናል ማለት 50,000 ብር ዋጋ ያለውን ኮምፒተር በ 75,000 ብር ሸጧል ማለት፣ ከመዝገብ ዋጋ በላይ (above book value) ስለሸጠ በ 75,000 ብር ላይ በሰንጠረዥ 'ሐ' መሰረት የንግድ ስራ ገቢ ግብር ይከፍላል።

  ምሳሌ፦**-2** ድርጅቱ በ 100,000 ብር የገዛውን እና 50,000 ብር የዕርጅና ቅናሽ የተደረገለትን ኮምፒተር በ 120,000 ብር ቢሸጠው፤

  120,000 - 50,000 = 70,000 በሰንጠረዥ 'ሐ' መሰረት የንግድ ስራ ገቢ ግብር 30 በመቶ ይከፍላል

2..1.የንግድ ስራ ገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ

- በድርጅቶች የሚከፈለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ 30 (ሰላሳ በመቶ) ነው።

- የግለሰቦች ግብር ማስከፈያ መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው።

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ በዓመት	ንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ	ተቀናሽ
0-24,000	0%	0
24,001-48,000	15%	3,600
48,001-84,000	20%	6,000
84,001-120,000	25%	10,200
120,001-168,000	30%	16,200
ከ 168,000 በላይ	35%	24,600

ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን የሚከተሉት ከጠቅላላ ገቢ ላይ ይቀነሳሉ

- በገቢ ግብር አዋጅ የተመለከቱ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ በንግድ ስራ ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ስራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ስራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፣
- በግብር ዓመቱ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ (trading stock) የወጣ ወጪ፣
- በንግድ ስራው ላይ ሲውሉ ዋጋቸው የሚቀንስ የንግድ ስራ ሃብቶችና ግዙፋዊ ህልወት ለሌላቸው የንግድ ስራ ሃብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣
- የንግድ ዕቃን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ በዓመቱ ውስጥ የንግድ ስራ ሃብትን በማስተላለፍ የገጠመው ኪሣራ።
- *በሠራተኛው የጤና ዕቅድ መሰረት ቀጣሪ በተቀጣሪ ስም የሚከፍለውን የጤናመድን አርቦን ጨምሮ ለሠራተኛው የሕክምና አገልግሎት የሚያወጣው ወጪ*

2..2.በታክስ ህጉ የተፈቀዱ ሌሎች ዝርዝር ተቀናሽ ወጪዎች

- *ድርጅቱ በነፃ በሚጠቀምበት ወይም በተከራየው ሀንፃ ሰራውን ሲያከናውን ቤቱን*

በሰጠው ወይም በአከራዩ ስም በሚታወቀው የመብራት፣ የውሃ ወይም የሰልክ ቆጣሪ የተጠቀመ እንደ ሆነ እነዚህ ክፍያዎች በግብር ከፋዩ እንደሚከፈሉ በግልፅ በውል ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ እና ወጪው የተከፈለበት ደረሰኝ ኦሪጂናል ካቀረበ፣

- *ለማዘጋጃ ቤት አገልግሎት የተከፈለ ክፍያ፣*
- *የተመዘገበ ኤክሳይዝ ታክስ እንዲሁም ተመላሽ ያልተደረገ ወይም*

በጊዜው ባለመቅረቡ ተመላሽ የማይደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ

- *የተበላሸ ዕቃ ዋጋ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸውና የተወገዱ እቃዎች ዋጋና ለማስወገድ*

የወጣ ወጪ፣

- *ግብር ከፋዩ ለንግድ ድርጅቱ እና መኖሪያ ቤት በአንድ የመብራትየሰልክ ወይም የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የመብራት፣ ሰልክ እና የውሃወጪ በወጪ ተቀናሽ የሚያዘው ከወጪው 75 በመቶ ብቻ ይሆናል።። ነገር ግን ወጪዎቹ ከሚያስገኘው ገቢ፣ ለሰራው ከሚሰጠው ዋስትና እና ቀጣይነት ጋር ሲነፃፀር ያልተጋነኑና ተመጣጠኝ መሆን አለበቸው።።*

  ለምሳሌ፦ ወጪን ከተገኘ ገቢ ጋር ማጣጣም (Matching priniciple) *በአመቱ መጨረሻ የአመቱን እንቅስቃሴ ያጠቃለሉ የሂሳብ መግለጫዎች ሲዘጋጁ በዓመቱ ውስጥ የተደረጉና በመዝገብ የሰፈሩ ወጭዎች ከዓመቱ ገቢ ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይም ገቢውን በማስገኘት ረገድ አስተዋጽኦ ወይም ተሳትፎ ያደረጉ መሆናቸው ተረጋግጦ ሊቀመጥ ይገባል።።ወጪዎቹ የተጋነኑ በሚሆኑበት ጊዜ ባለስልጣኑ በተገቢው መረጃ ላይ ተመስርቶ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።።*

- *አንድ ግብር ከፋይ የንግድ ስራ እንቅስቃሴው በተቋረጠበት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወይም ስራ ባላገኘበት ጊዜ ያወጣው ወጪ የማይቀር ወጪ ሆኖ ከተገኘ ገቢ ያላስገኘ ወጪ ቢሆንም በወጪ ተቀናሽ ሊፈቀድለት ይችላል።።*

  ለምሳሌ፦ የቤት ኪራይ ፣የሰራተኛ ደመወዝ፣ መብራት፣ውሃ፣ስልክ፣የመሳሰሉት ወጪዎች ሊሆኑ ይችላሉ

- ***ግለሰብ የንግድ ሰራ ባለሀብት ከመደበኛ የሥራ ቦታው ከ***25 ***ኪሎ ሜትር በላይ በመሄድ የንግድ ሰራውን ለማከናወን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለሚያወጣቸው ወጪዎች ለምግብ እና ለመኝታ ለአንድ ቀን እስከ*** 1000 ***ብር ይፈቀድለታል። በተጨማሪም ለትራንስፖርት ያወጣው ወጪ. በስራ ላይ ባለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ መሰረት በማስረጃ ተረጋግጦ የወጪ. ተቀናሽ የሚፈቀድለት ሆኖ ከዚህ መጠን በላይ የሚያወጣው ወጪ. በተቀናሽ ወጪ. አይያዝም።***
- ***"የውክልና ወጪ.***(representation allowance) ***ማለት የግብር ከፋዩ ሠራተኛ የንግድ ሥራውን ለማስተዋወቅና ለማሳደግ እንግዶችን ከንግድሥራ ቦታው ውጪ. ለመቀበል የሚያወጣው ወጪ. ነው። በዚህም መሰረት (መሥሪያ ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኝ ተቀጣሪ ከተቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ*** 10 ***በመቶ) ለግብር ከፋዩ ሠራተኛ የሚከፈል የኃለፊነት አበል ወይም የውክልና አበል ተቀናሽ ሊሆን የሚችለው የንግድ ሰራውን የማስተዋወቅ እና የማሳደግ ስራ ላይ በሃላፊነት ለሚሰራ ሰራተኛ ወይም የስራ መሪ የተከፈለ ሲሆን ነው ይህም በወጪ. ማስረጃ የተረጋገጠ ሊሆን ይገባዋል።***
- ***ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅት በስራ ላይ ለሰማራው አባሉ የሚከፍለው ደመወዝ እንደ ወጪ. ተቀናሽ ይፈቀድለታል።***
- ***በዲዛይን ለውጥ ምክንያት ሀንጻ ፈርሶ ሲገነባ የፈረሰው ሀንፃ የመዘገብ ዋጋ በውጪ. ተቀናሽ ይያዛል።***
- ***የተሸከርካሪ ጎማ የሚሰጠው አገልግሎት ከአንድ ዓመት ያነሰ እንደሆነ እንደ አላቂ ዕቃ ተቆጥሮ በተቀናሽ ወጪ. የሚያዝ ይሆናል።***
- በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድ ስራ ሀብት የሚፈጸም የኪራይ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።በዚህ መሰረት ተቀናሽ የተፈቀደለት ሰው በንብረቱ ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሰብለትም።

3.3.1.1. ውጭ ሃገር የሚገኝ የዋናው መስሪያ ቤት ወጪ.

- ***በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው በቋሚነት ለሚሰራ ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ. ለመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሰራው ድርጅት የሚፈጽመው ክፍያ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪው የንግድ ስራ ገቢ ለማግኘት፣ለንግዱ ስራ ዋስትና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የተደረገ እና በቋሚነት በሚሰራው ድርጅት ሊሰራ የማይችል ከሆነ ብቻ ነው።***

3.3.1.2. የወለድወጪ.

የወለድ ወጪ. በተቀናሽነት የሚያዘው

- ብድሩ የንግድ ስራ ገቢን ለማግኘት ከዋለ፣ ወይም ***የወለድ ወጪ. በብድሩ የተገኘው ገንዘብ ለንግድ ስራ እንቅስቃሴ መዋሉ ሲረጋገጥ ነው።***
- ብድሩየተገኘው የብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጠው የፋይናንስ ተቋም ወይም ብድር እንዲሰጥ ከተፈቀደለት የውጭ አገር ባንክ ከሆነ
- ከተፈቀደለት ባንክ ለተወሰደ ብድር የተከፈለ ወለድ ያለገደብ ይቀነሳል።
- ብድሩ የተገኘው የብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጠው የፋይናንስ ተቋም ወይም ብድር እንዲሰጥ ከተፈቀደለት የውጭ አገር ባንክ ከሆነ
    - ✓ ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው አበዳሪው ብድር ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኘበትን ሰነድ ቅጂ ለባለሥልጣኑ ካቀረበ ብቻ ነው።

- የብድር ወለድ መክፈል የሚቻለው በብሄራዊ ባንክና በንግድ ባንክ መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ ምጣኔ ከ 2% ባልበለጠ ነው ።

<u>ለምሳሌ</u>

- ከእህት ኩባንያ (Sister Campany)፣ ከሼር ሆልደር ወይም ከግለሰብ ለተወሰደ ብድር ወለድ መክፈል የሚቻለው ብሄራዊ ባንክና ለንግድ ባንኮች ብድር ሲሰጣቸው ንግድ ባንኮች ለብሄራዊ ባንክ የሚከፍሉት ወለድ ላይ 2% ጨምሮ መክፈል ይችላል። በዚሁ መሰረት ብሄራዊ ባንክ ለንግድ ባንኮች ብድር ሲሰጣቸው 10% ወለድ የሚያስከፍላቸው ቢሆን ከላይ ከጠቀስናቸው አበዳሪዎች ገንዘብ የተበደረ ድርጅት ንግድ ባንኮች ለብሄራዊ ባንክ የሚከፍሉት ወለድ 10% ላይ 2% ጨምሮ መክፈል ይችላል። በተጨማሪም ተበዳሪው ድርጅት ከእህት ኩባንያ (Sister Campany) ፣ ከሼር ሆልደር ወይም ከግለሰብ ለተበደረው ገንዘብ ከላይ በተቀመጠው ምሳሌ መጠን የከፈለው የወለድ ወጪ በወጪነት ሊያዝለት የሚችለው ከሚከፈለው ወለድ ላይ 10% ግብር ቀንሶ ካስቀረ ነው።
- ***የፋይናንስ ተቋማትን ሳይጨምር አንድ ግብር ከፋይ ለተወሰነ የስራ እንቅስቃሴ የወሰደውን ብድር ለሌላ ዓላማ የሚያውል ወይም ይሀንኑ ብድር ለሌላ ተግባር በብድር የሰጠ ከሆነ፣ የሚፈቀድለት ተቀናሽ የወለድ ወጪ ለሌላ ያበደረው ወይም ለሌላ ዓላማ ያዋለው ተቀንሶ ለንግድ ስራው እንቅስቃሴ በዋለው ብድር መጠን ብቻ ይሆናል።***
- ***አንድ ግብር ከፋይ በዱቤ ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋውን እስኪከፍል ድረስ ወለድ እንደሚከፈልበት ውል የገባ እንደሆነ ለከፈለው የወለድ መጠን የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል።***
- ***ግብር ከፋይ ሀንጻ ለመገንባት ብድር የወሰደ እንደሆነ ሀንፃው እስኪጠናቀቅ ድረስ የተከፈለው ወለድ በእርጅና ተቀናሽ የሚካተት ሆኖ ሀንጻው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኋላ የተከፈለው ወለድ በወጪ ተቀናሽ የሚፈቀድ ይሆናል።***

3.3.1.3. ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተደረገ ስጦታ፣

- ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተደረገ ስጦታ በወጪነት የሚያዘው፣

- *መንግሥት ባደረገው ጥሪ መሠረት ለልማት፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር፣ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ወይም ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት የተደረገ ስጦታ ከሆነ ተቀናሽ ይደረጋል።*
- በመንግስት የተደረገ ጥሪ ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት የሚደረግ ጥሪ ሲሆን በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚደረግ ጥሪን ይጨምራል።
- በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በተሰጣቸው ትርጉም መሰረት ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ለኢትዮጵያ ማኅበር የተሰጠ ሲሆን ወይም
- ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች የተፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ግብር ከፋዩ ራሱ ለሚያካሂደው የበጎ አድራጎት ተግባር ለሚያውለው ወጪ ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል።
- የበጎ አድራጎት ተግባር ማለት፡- ከታክስ ከፋይ ሠራተኞቹ ውጭ ለሌሎች ተረጂዎች የሚሰጥ የትምህርት የጤና የአካባቢጥበቃ ወይም ሌላ ሰብአዊ እርዳታ ነው።
- የሚፈቀደው ጠቅላላ የስጦታ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ 10% (አሥር በመቶ) የበለጠ አይሆንም።

- ***ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ ማለት ለበጎ አድራጎት ስራ የተደረጉ ስጦታዎች ሳይቀነሱ በሂሳብ መዝገቡ የታየው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው።***

3.3.1.4. በታክስ ህጉ የተፈቀዱ የእርጅና ቅናሽ አሠራር

ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ለማድረግ ይፈቀድለታል።የእርጅና ቅናሹን ለማወቅ እና ለማስላት የሚከተሉትን ቃላቶች ትርጉማቸውን መረዳት ያስፈልጋል በዚህም መሰረት፡-

1. ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሃብቶች ማለት፡-

- የቅጅ መብት፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ ምስጢራዊ ቀመር ወይም የአሠራር ሂደት፣ የንግድ ምልክት፣ ወይም ለተወሰነ ዘመን ብቻ የሚያገለግል ሌላ ተመሳሳይ ሀብት፤
- የደንበኞች ዝርዝር፣ የሥርጭት መስመር ወይም የተለየ ስም፣ ምልክት ወይም ስዕል ወይም ለተወሰነ ዘመን ብቻ የሚያገለግል ሌላ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ዘይቤ፤
- ከአንድ ዓመት በላይ ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ የሚያገለግል ከውል የሚመነጭ መብት (ወጪውአስቀድሞ የተከፈለንም ጨምሮ)፤
- ማንኛውንም ግዙፋዊ ሀልዎት ያለውን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ሀብት ለማግኘት የወጣን ወጪሳይጨምር፣ ከአንድ ዓመት በላይ ጥቅም የሚሰጥ ወጪ፤

2. ዋጋው የሚቀንስ ሀብትማለት፡-

- ከአንድ ዓመት የሚበልጥ የአገልግሎት ዘመን ያለው፤
- በእርጅና ወይም ጊዜው በማለፉ ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ የሚችል፤
- በከፊል ወይም በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋለ፤
- ግዙፋዊ ሀልዎት ያለው የሚንቀሳቀስ ሀብት ወይም በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ነው፡-

- በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ማለት፡- ቤት ወይም ሌላ የቤቱ አካል የሚሆን ወይም ከቤቱ ጋር ለዘለቄታው የተያያዘ በቤቱ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጭማሪ ወይም ለውጥ ሲሆን መንገድን፣ መጋቢ መንገድ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ አጥር ወይም ግንብን ይጨምራል።
- ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች አመቱን በሙሉ የንግድ ስራ ገቢን ለማግኘት ጥቅም ላይ ያልዋሉ እንደሆነየእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ሀብቶቹ ጥቅም ላይ ያልዋሉበት ዓመት ሂሣብ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ከተቀነሰ በኋላ ነው።
- ለግብር ዓመቱ ከፊል ጊዜ አገልግሎት የሰጠ ወይም በከፊል ለንግዱ ስራ በከፊል ደግሞ ለሌላ ስራ የዋለ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብትለንግድ ስራ በዋለበት መጠን ብቻ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል።
- እርጅናቅናሽ መታሰብ የሚጀምረው ዋጋው የሚቀንስ ሃብት ሀንጻ ከሆነ የሀንጻ ግንባታ መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን በፊት ሊሆን አይችልም። ሌላ ሀብት ከሆነ ለንግድ ስራ ዝግጁ ከሆነበትና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል።

- በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ ለሚደረግ ማሻሻያ ወጪ የእርጅና ቅናሽ ሲሰላ ማሻሻያው ያረፈበትን መሬት ወጪ መጨመር የለበትም።
- የንግድ ሥራ ሀብት ማስተላለፍ፦
  - አስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ያገኘበትን የንግድ ሥራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው አስተላልፎ እንደሆነ የተላለፈለት ሰው የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም።
  - ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተላለፈው ሀብት የእርጅና ቅናሽ ጊዜውን ያልጨረሰ ከሆነና የተላለፈበት ዋጋ ከቀሪ የመዝገብ ዋጋው የበለጠ እንደሆነ የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሚሆነው ቀሪ የመዝገብ ዋጋው ነው።
  - በዓይነት ለሚደረግ የካፒታል ሀብት መዋጮ እና በውርስ ለሚተላለፍ ሀብት የእርጅና ቅናሽ መሰረት የሚሆነው ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ የነበረው ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ነው።

3.3.1.5. የእርጅና ቅናሽ ስሌት ዘዴዎች

- ግብር ከፋይ ለግብር አከፋፈልና ለሌላ አላማ ለሚያዘጋጃቸው የሂሣብ ሪፖርቶች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጠቀም አለበት ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች ሁሉ መጠቀም ያለበት አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ነው

➢ ሁለት አይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን

  ✓ ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ እና
  ✓ ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ በመባል ይታወቃሉ።

➢ ታክስ ከፋዮች የሚፈቀድላቸውን የእርጅና ቅናሽ በቀጥተኛ ወይም ዋጋው እየቀነሰ በሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት ሊወስኑ ይችላሉ።

3.3.1.6. ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

- የሚከተሉት ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ መሰላት ያለበት በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ብቻ ይሆናል።
  - ➢ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች፣
  - ➢ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ፤
    - ✓ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ የእርጅና ቅናሽ ሲሰላ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ወጪ ማሻሻያው ያረፈበትን መሬት ወጪ መጨመር የለበትም።
    - ✓ ማንኛውም ግብር ከፋይ "አስተላላፊ" ተብሎ ከሚጠራ ግንኙነት ያለው ሰው ላገኘው እና በአስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ላገኘበት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም ።
    - ✓ ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የተፈቀደው በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በሀብቱ ወጪ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል።

3.3.1.7. ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ

- ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የተፈቀደው ዋጋው እየቀነሰ በሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በዓመቱ መጀመሪያ ባለው የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል።
- በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ከሆነ፣የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ብቻ ጥቅም ላይ እንደዋለ በመውሰድ ይሰላል።
- የግብር ከፋዩ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከብር ሁለት ሺህ በታች ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት ይያዛል።
- ***ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ መጠን የሚሰላው በግብር ዓመቱ መጀመሪያ በነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ የእርጅና ተቀናሽ መጣኔውን በማስላት ይሆናል።***
  - ***በግብር ዓመቱ መጀመሪያ የነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ማለት፡- ከመጀመሪያው የመዝገብ ዋጋ በየጊዜው የተቀነሱ የእርጅና ተቀናሾች ከተቀነሰ በኋላ የሚገኝ ዋጋ ነው።***

3.3.1.8. የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች

- ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች በሚከተሉት ምድቦች መሠረት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ተዘርዝረዋል

ዋጋው የሚቀንስ ሀብት	የቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጣኔ	ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅ ናቅናሽ ዘዴ መጣኔ
ኮምፒውተር፣ሶፍትዌር እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያ	20 በመቶ	25 በመቶ
ግሪንሃውስ	10 በመቶ	-
ግሪንሃውስን ሳይጨምር በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ	5 በመቶ	-
ሌላ ማንኛውም ዋጋው የሚቀንስ ሀብት	15 በመቶ	20 በመቶ
ለማዕድንና ነዳጅ የልማት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውል ዋጋው የሚቀንስ ሀብት	25 በመቶ	30 በመቶ

- ***ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች (የፈጠራ መብት ባለቤትነት***(copy Right)***፣መልካም ዝና*** (Good Will) ***የንግድ ምልክት***(TradeMark) ***ለመሳሰሉት*** ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ

ሀ) የንግድ ስራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ ሃያ አምስት 25 % በመቶ፣

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከአስር ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት አስር 10 % በመቶ፣ ወይም

ሐ) ለሌላ ማንኛውም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት መቶበመቶ 100%ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌለው ሀብት የአግልገሎት ዘመን በማካፈልየሚገኘውመጣኔ፣ይሆናል።

- የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ ማለት፡- ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያወጣውግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች የተመለከተው ወጪ ነው።

- በከፊል ለንግድ ስራ በዋለ ሕንጻ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ በተመለከተ አንድ ሕንጻ በንግድ ሥራ ሀብትነት በከፊል በሚያገለግልበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ስራ አገልግሎት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል።

የመከራ ጥያቄ ሶስት

1 ኛ. ስንት አይነት የዕርጅና ቅናሽ ዘዴዎች አሉ? ዘርዝሩ በምሳሌም አሳዩ

ምሳሌ፦-

ሃብቱ 1 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሲሆን የመጠቀሚያ ጊዜው ለ 5 አመታት ነው ይህ ሃብት በአመት 20 በመቶ ዋጋው ይቀንሳል ተብሎ ቢታሰብ በአምስት አመቱ መጨረሻ ላይ የሃብቱ ዋጋ ምንያህል ይሆናል? በቀጥተኛ የዕርጅና ቅናሽ ዘዴ አስሉ

አመት	የሃብቱ ዋጋ	የሚቀንሰው የዋጋ መጠን **(depreciation rate)**	የመጨረሻው የመዝገብ ዋጋ
1	1000,0000	200,000	800,000
2	800,000	200,000	600,000
3	600,000	200,000	400,000
4	400,000	200,000	200,000
5	200,000	200,000	0

2..3.ጥገናዎችና ማሻሻያዎች ላይ የሚደረግ የወጪ ተቀናሽ

- ማንኛውም ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል።
  - የሚፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ሀብቱ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ካለው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሃያ በመቶ (20 %) ፣ ሊበልጥ አይችልም።
  - በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ የተደረገ የጥገና ወይም የማሻሻያ ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሃያ በመቶ የሚበልጥ ከሆነ የጥገናው ወይም የማሻሻያው ሙሉ ወጪ በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ይጨመራል።
- ***ማንኛውም ግብር ከፋይ "አስተላላፊ" ተብሎ ከሚጠራ ግንኙነት ካለው ሰው ላገኘውና በአስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ላገኘበት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም።ሆኖም ጊዜያቸውን ያልጨረሱ ንብረቶች ሽያጭ የተከናወነው ግንኙነት ባላቸው መካከል ከሆነና የተላለፈበት ዋጋ ከተጣራ የመዝገብ ዋጋው የሚበልጥ ከሆነ የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሚሆነው የተጣራ የመዝገብ ዋጋው ነው።***
- ***በግብር ከፋዩ የተገነባ ለንግድ ስራ ጥቅም ላይ የዋለው የህንፃ ክፍል የእርጅና ቅናሽ መታሰብ የሚጀምረው ሀብቱ የንግድ ስራ ገቢውን ለማስገኘት ለአገልግሎት ዝግጁ ከሆነበት እና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን አንስቶ***

ሲሆን ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ለግብር ከፋዩ የሀንፃ ግንባታው ስለመጠናቀቁ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ከሰጠበት ጊዜ በፊት ሊሆን አይችልም።

- አንድ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት በግብር ዓመቱ ከፊል ለሆነው የዓመቱ ጊዜ ብቻ በጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ የሚፈቀደው የእርጅና ተቀናሽ ወጪ ከጠቅላላ የዓመቱ የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ ላይ ጥቅም ላይ ያልዋለበት የዓመቱ ከፊል ጊዜ ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ከተቀነሰ በኃላ ያለው ተቀናሽ ወጪ ብቻ ነው።
- ለንግድ ስራ የተገነባ አንድ ሀንፃ በንግድ ሥራ ሃብትነት በከፊል በሚያገለግልበትጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ሥራ አገልግሎት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል።
- ለእርጅና ተቀናሽ አያያዝ ከጠቅላላው የሀንፃ ስፋት ዋጋ ለንግድ ስራ ጥቅም ላይ የዋለው የሀንፃው መጠን ዋጋ ተለይቶ ካልቀረበ በወለሉ ስፋት መቶኛ በማስላት ዋጋው ተለይቶ መቅረብ አለበት።
- ለንግድ ስራ ጥቅም ላይ ያልዋለውን የሀንጻ ክፍል ግበር ከፋዩ ለይቶ ካለቀረበ ከጠቅላላ የሀንጻው ዋጋ ለንግድ ስራው የዋለውን የሀንፃው ስፋት መጠን በማስላት ባለስልጣኑ በራሱ ወሰኖ ተቀናሽ ያደርጋል።
  - ጥቅም ላይ የዋለ የሀንፃ ክፍል ማለት የሀንፃው ክፍል ለሌላ ዓላማ እስካልዋለ ድረስ ግብር ከፋዩ ሀንፃውን ለኪራይ አገልግሎት ዝግጁ ያደረገ ከሆነ ሀንፃው ባይከራይም ለኪራይ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዳዋለ ተቆጥሮ ከቤት ኪራይ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር በሚሰላበት ጊዜ እንደወጪ ተቀናሽ ሊያዝለት ይገባል።
- የአንድ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ለማስላት መሰረት የሆነው የተሰራበት ወይም የተገዛበት ዋጋ የሚገልጽ ሰነድ ታክስ ከፋዩ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለስልጣኑ የተሰራበት ወይም የተገዛበት የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ 70 በመቶ የእርጅና ተቀናሽ ይፈቀድለታል።ሀብቱ የተገዛበት ወይም የተሰራበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ታክስ የተካካሰለት ከሆነ የተካካሰው (የተቀናነሰ) መጠን በሚፈቀድለት የእርጅና ተቀናሽ ዋጋ ውስጥ አይካተትም።
- በባል/በሚስት ስም የተመዘገበ ሀንጻ ለግለሰቡ ንግድ ስራ የዋለ እንደሆነ የእርጅናተቀናሽሊፈቀደ የሚችለው ሀንፃው ለንግድ ስራው አገልግሎት እንዲውል ፤የእርጅናተቀናሽ እንዲጠየቅበት፤ ሀንፃው ሲሸጥ ተገቢውን ግብርና ታክስ እንዲከፈልበት የባልና የሚስት የስምምነት ሰነድ ሲቀርብ ነው።
- ለቀጥተኛ የእርጅና ተቀናሽ የግብር ከፋዩ ዋጋውየሚቀንስሀብትወይም ማዙፋዊ ሀለዎት ለሌለው የንግድ ስራ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከ2 ሺ የሚበልጥ ከሆነ የእርጅና ተቀናሽ ይፈቀድለታል
- ማንኛውም የንግድ ስራ ሀብት የተናጠል ዋጋከብር ከ2000 (ሁለት ሺ) በታች ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት መያዝ አለበት
- የካፒታልሀብት በማሰስተላለፍ በሚገኝ ጥቅምላይ ለሚከፈል ግብር አለማምዝገባ የሚፈፀምበት ሀብት በሽያጭ በልውውጥ ወይም በስጦታ ሲተላለፍ አስተላላፊው ሀብቱን እንዲያስተላለፈ የሚቆጠረው እና የተላለፈበት ሰው ሀብቱን በባለቤትነት እንደያዘ የሚቆጠረው የሽያጭ፤ የልውውጥ ወይም የስጦታ ውሉ ፣ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ከተመዘገበበትቀን ጀምሮ ሆኖ የእርጅና ተቀናሽ ሊጠየቅ የሚችለው ሀብቱ የተመዘገበ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።
- በታክስ ከፋዩ ስም ለልተመዘገቡ ሀብቶች የእርጅና ተቀናሽ ወጪ አይፈቀድም።

- በዓይነት የሚደረግ የካፒታል ሀብት መዋጮ እና በውርስ ለሚተላለፍ ሀብት የእርጅና ቅናሽ መሰረት በሚተላለፍበት ጊዜ በነበረው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው።

2..4.የማስታወቂያ ወጪ.

- የንግድ ሰራ ለማስተዋወቅ የተደረገ ወጪ. በወጪነት የሚያዘው፡- ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ ለመገናኛ ብዙሀን ወይም ለማስታወቂያ ድርጅት የሚከፍለው ክፍያ ሙሉ በሙሉ በወጪ ተቀናሽነት ይያዛል።
- ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የሚያደርገው የማስተዋወቅ ሰራ በገንዘብ ወይም በምርት ወይም በአገልግሎት የሚፈጽመው ክፍያ በወጪ. ተቀናሽ የሚያዘው ከጠቅላላ ገቢው 3% በመቶባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።
- ምንም የማስተዋወቅ ሰራ ሳይሰራበት የሚሰጥ ገንዘብ፣ ምርት ወይም አገልግሎት ክፍያ በማስታወቂያ ወጪ. ተቀናሽ ሆኖ አይያዝም።

2..5. በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት የሚያጋጥምን ብክነት እንደ ወጪ ስለመያዝ

- በምርት ዝግጅትና አቅርቦት ሂደት (ሰሊጥ እና ኑግበብጣሪ፤በትነት ነዳጅ ፤ በማቅለጥ፣ በሸርፍራፊ፣ ቡና በቆይታ ጊዜ ወዘተ) የሚባክን ምርት በሚመለከተው የመንግስት አካል በቀረበ ጥናት መሰረት እንደ ወጪ ሊያዝ ይችላል። የተሟላ ጥናት ማግኘት ካልተቻለ ባለስልጣኑ ከግል ተቋማት ከግብር ከፋዮች አማባብነት ያለው አካል ወይም ባለስልጣኑ በሚያደርገው ጥናት መሰረት ወጪ. የሚያዝበትን መጠን ሊወስን ይችላል። ለእያንዳንዱ ምርት መረጃ ሊሰጥ የሚገባውን አማባብነት ያለውን አካል ባለስልጣኑ ይወስናል።

2..6.ተቀናሽ የሚደረግ የመዝናኛ ወጪ.

- መዝናኛ ማለት፡-ለማንኛውም ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትምባሆ፣ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ሲሆን ሆቴልች፣ሬስቶራንቶችወይም የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለሠራተኞቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ወጪ.ተቀናሽ የሚደረገው ከታች በተገለጸው መሰረት ይሆናል።

1. የማዕድን ማውጣት እና ፍለጋ፤ የማኑፋክቸሪንግና የግብርናና ሆርቲ ካልቸር ሰራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ ዋጋበወጪ. የሚያዘው በአንድ ወር የሚያወጣው ወጪ. በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ካወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ. ከ 30% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው።
2. ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ወይም ሌሎች የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋማት ውስጥ ለተሰማሩ ሰራተኞች ለቀጣሪዎች የሚያቀርቡት የምግብ እና መጠጥ ወጪ. ተቀናሽ የሚያደርገው በአንድ ወር የወጣው ወጪ. በወሩ ለተቀጣሪዎቹ ከወጣው አጠቃላይ የደሞዝ ወጪ. 20% ያልበለጠ መጠን ብቻ ነው።

- ለመጠጥ የሚፈቀደው ተቀናሽ ወጪ. ምንም አይነት የአልኮል ይዘት የሌለው መጠጥ ነው
- ከላይ በተራቁጥር 1 እና 2 የተገለጹት ድርጅቶች የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡት በራሳቸው አዘጋጅተው ከሆነ ከምግብ ዝግጅት ጋር በተያያዘ የተደረጉት የግብዓት ወጪዎች በወጪ. ተቀባይነት አግኝተው ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው ከድርጅቱ በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ ወይም የግዢ ማስረጃ መሰረት ይሆናል።

- *በተራ ቁጥር 1 የተገለጹት ተቋማት የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡት በ3ኛ ወገን አማካኝነት ከሆነ ወጪው ተቀባይነት የሚኖረው ስለአቅርቦቱ ከአቅራቢው ጋር የተደረገ ውል አገልግሎቱ ስለመገኘቱ ከድርጅቱ በሚቀርብ ማረጋገጫ እና ለአቅራቢው ገንዘቡ ስለመከፈሉ በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ መሰረት ይሆናል።*
- *በማዕድን ማውጣት በማኑፋክቸሪንግ እና በግብርና እና በሆርቲካልቸር ስራ የተሰማራ ቀጣሪ ከከተማ ርቆ በሚገኝ ቦታ ለተመደበው ተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው የማረፍያ ቤት አገልግሎት ያወጣው ወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል።*
    - ✓ *ከከተማ ርቆ የሚገኝ ቦታ ማለት ቢያንስ ሃያ ሺህ ነዋሪ ካለው የከተማ ወሰን ሰለሳ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ሥፍራ ነው።*

2..7.የማይሰበሰብ ዕዳ

- የማይሰበሰብ ዕዳ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ፦
    - ዕዳው ቀደም ሲል የንግድ ስራ ገቢ ሆኖ ተይዞ /ተመዝግቦ/ ከሆነ፣
    - ዕዳውን ለማስከፈል አስፈላጊ የህግ እርምጃ ተወስዶ ማስመለስ ያልተቻለ እንደሆነ ነው፣
    - ዕዳው ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የተሰረዘ እንደሆነ፣ እና
    - የሚቀነሰው የዕዳ መጠን ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ከተሰረዘው የዕዳ መጠን መብለጥ የለበትም።
    - ይህ ተቀናሽ ለፋይናንስ ተቋማት ተፈፃሚ አይሆንም።

2..8.ኪሳራ

1. ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ኪሳራ ካጋጠመው፣ በግብር ዓመቱ የደረሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ለማሸጋገር ይችላል፤ ስለሆነም የግብር ከፋዩ የሚቀጥለው ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የተሸጋገረው ኪሳራ በተቀናሽነት ይያዛል።
2. ኪሣራ ሊሸጋገር የሚችለው ኪሣራውን የሚያሳየው የግብር ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ኦዲት የተደረገ እና በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው።

- ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና ሁለት የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዩ፦-

ሀ) ኪሣራ የሚያሳየውን በውጪ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ የሒሣብ መዝገብ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ እንደሆነ፣ እና

ለ) የቀጣዩ የግብር ዓመት የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ የግብር ከፋዩን የሂሣብ መዝገብ ኦዲት ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣ኪሣራውን ሊያሸጋግር ይችላል።

- ኪሳራ ለማሸጋገር የሚቻለው ኪሳረው ከደረሰበት ዓመት ቀጥሎ ላሉት አምስትዓመታትነው፣
- ኪሳራ ለማሸጋገርና በወጪነት ለመያዝ የሚፈቀደውም በንግድ ስራ ዘመኑ (በህይወት) ዘመኑ ለሁለት የግብር አመታት ብቻ የደረሰ ኪሳራ ነው።
- አንድ ግብር ከፋይ የሚሸጋገርኪሳራ ከአንድ የግብር ዓመት በላይ ያጋጠመው ከሆነግብር ከፋዩ መጀመሪያ የገጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይቀነስለታል።

- የታክስ ባለሥልጣኑን በታክስ አዋጅ መሰረት የግብር ከፋዩን ኪሳራ በመመርመር የተሻሻለ የግብር ስሌት ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ የመስጠት መብት አለው።
- ከረጅም ጊዜ ውልጋር ተያይዞ የሚያጋጥም ኪሳራ ተካክሶ እስከ ሚያልቅ ድረስ ወደ ታላ ሊሸጋገር ይችላል።

2..9.ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች ኪሣራ መጠባበቂያ

- የባንኮች ኪሣራ መጠባበቂያ

- ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሣራ የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ሂሣብ በተቀመጠ የጥንቃቄ መሥፈርት መሠረት እስከተሰላ እና ከፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ በግብር ዓመቱ የመጠባበቂያ ሂሣቡ መጠን ሰማንያ (80) በመቶ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል።

- የጠቅላላ መድን ኩባንያዎች ጊዜው ያላለፈ ሥጋት መጠባበቂያ

- ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ በአንድ የግብር ዓመት ጊዜው ላላለፈ ሥጋት የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን በሂሣብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ እስከሆነ ድረስ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚታየው ቀሪ የመጠባበቂያ ሂሣብ ለግብር ዓመቱ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ የመድን ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የመድን ሥራ የሚሠራ ከሆነ በተቀናሽ ወጪ የሚያዝለት መጠን ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ጊዜው ላላለፈ ሥጋት በያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ የተወሰነ ይሆናል።

- ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ንግድ ሥራ ገቢ እንደ ባለፈው የግብር ዓመት በተቀናሽ ወጪ የተያዘለትን ጊዜያቸው ላላለፈ ሥጋቶች የያዘውን የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ይጨምራል።

- ጠቅላላ መድንማለት በንግድ፥-በሕግ ከተገለጸው የሕይወት መድን በስተቀር ማንኛውም መድን ነው።

2..10. የህይወት መድን ንግድ ሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ

- የህይወት መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል።(ህ+ለ+ሐ+መ) -(ሠ+ረ+ሰ+ሸ) ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፥-
  - "ህ". የህይወት መድን ለገዙ ደንበኞች ኩባንያው የመለሰውን አረቦን ሳይጨምር በአንድ ዓመት ውስጥ ያገኘው የህይወት መድን አረቦን
  - "ለ". በዓመት ውስጥ ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ ኩባንያው ያገኘው የኢንቨስትመንት ገቢ
  - "ሐ". በዓመቱ ለተሰረዙ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ኩባንያው ባለፉት ጊዜያት በተቀናሽ ወጪ.የተያዘለት ማናቸውም የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን፣
  - "መ". ኩባንያው በዓመቱ ከህይወት መድን ሥራ ያገኘው ሌላ ማንኛውም ገቢ፣
  - "ሠ". ኩባንያው ከሚያካሂደው የህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ የኮሚሽንክፍያዎችን፣የጠለፋ ዋስትና አረቦንን፣ የሥጋት ትንተና ወጪዎችን፣በፖሊሲው ላይ የሚጠየቁየመንግሥትክፍዎችን እናየሥራ ማስኬጃወጪዎችን ጨምሮ በዓመቱ ከመድን ፖሊሲያቸጋጋር በተያያዘያወጣው ወጪ፣

- "ረ". በዓመቱ ላወጣቸው አዲስ የህይወት መድን ፖሊሲዎች የያዘውን መነሻ የመጠባበቂያ ሂሣብ ጨምሮ የያዘው ተጨማሪ የህይወት መድን ፖሊሲ መጠባበቂያ ሂሣብ፣
- "ሰ". በዓመቱ ከተከፈሉ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ጋር በተገናኘ ከያዘው ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን እና በዚሁ ሂሣብ ላይ ካገኘው ገቢ በላይ በህይወት መድን ፖሊሲዎች መሠረት ለቀረቡ የህይወት መድን ክፍያ ጥያቄዎች የፈፀመው ክፍያ፣እና
- "ሸ". ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተገናኘ ኩባንያው በዓመቱ ውስጥ ያወጣውሌላ ማንኛውም ተቀናሽ ወጪ ነው።

✓ አንድ ኩባንያ ከህይወት መድን ሥራ በተጨማሪ የጠቅላላ መድን ሥራን ጨምሮ በሌላማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ እንደሆነ ከህይወት መድን ሥራ የሚያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከሌላው የንግድ ሥራ ገቢው ተለይቶ ለብቻው መሰላት አለበት።

✓ የህይወት መድን በንግድ ሕግ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

2..11. ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች እና ኪሳራዎች

❑ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ አይያዙም፡-

ሀ. የካፒታልነት ባህርይ ያላቸው ወጪዎች፤

ለ. የኩባንያ አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ፤

ሐ. ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ 15% (አሥራ አምስት መቶኛ) በላይ በፈቃደኝነት የሚደረግ የጡረታወይም የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ፤

መ)የአክሲዮን ድርሻ እና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል፤

ሠ)በመድን፣ በካሳ ወይም በዋስትና ውል መሠረት የተመለሰ ወይም ሊመለስ የሚችል ወጪወይም ኪሳራ፤

ረ)ማንኛውንም ሕግ ወይም ውል በመጣስ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ወይም የሚከፈል ካሳ፤

ሰ)ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ የሚያዘው በወቅቱ ወጪያልተደረገ ነገር ግን ለወደፊት በግብር ዓመቱ ለሚከሰቱ ወጪዎችወይም ኪሳራዎች መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ የሚያዝ ገንዘብ ወይም የመጠባበቂያ ሂሣብ፤

ሸ)በገቢ ግብር አዋጅ ወይም በውጭ ሀገር የታክስ ሕግ መሠረት የተከፈለ የገቢ ግብር ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

ቀ) ***ለግብር ከፋዩ ሠራተኛ የሚከፈል የኃላፊነት አበል ወይም የውክልና አበል ተቀናሽ ሊሆን የሚችለው የንግድ ሰራውን የማስተዋወቅ እና የማሳደግ ሰራ ላይ በሃላፊነት ለሚሰራ ሰራተኛ ወይም የስራ መሪ የተከፈለ ሲሆን*** 10 ***በመቶ በላይ የተከፈለ ክፍያ በተቀናሽነት አይያዝም።***

❑ ከሚከተሉት በስተቀር ለመዝናኛ የሚወጣ ወጪ፤

I. የግብርከፋዩ የንግድ ሥራ የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት ሲሆን፤ወይም

II. ሚኒስቴሩ በመመሪያ ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግወይም በግብርና ሥራ የተሠማራ ቀጣሪ ሠራተኞቹን ለማዝናናት የሚያወጣው ወጪ፤

ተ)በአዋጁ መሰረት ለበጎ አድራጎት ከሚሰጥ ስጦታ ውጭየሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

ቸ)ግብር ከፋዩ ለራሱ የሚያወጣው የግል ውጪ፤

ኀ) ግብር ከፋዩ አንድን የንግድ ሥራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ የሚደርስ

ኪሳራ፤

ነ) መዝናኛ ማለት፡- ለማንኛውም ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትንባሆ፣ ማረፊያ፣ መደሰቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ነው።

የመከራየቂ አራት

1. የማይሰበሰብ እዳ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ምን፤ምን መስፈርቶች ሲሟሉ ነው?
2. በአንድ የግር ዘመን ኪሳራ የገጠመው ሰው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው ለስንት አመታት ነው?

ክፍል አራት

3. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ ዓመት

- የራሱን የሂሳብ አመት እንደ ግብር አመት እንዲጠቀም ፈቃድ ለተሰጠው ግለሰብና ድርጅት የሂሳብ ዓመት ነው የሚባለው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሂሳብ ሚዛን(Balancesheet) በሚዘጋበት ጊዜ የሚጠናቀቀው የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ነው።
- ማንኛውም ግብር ከፋይ ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝና ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያሟላ የሂሳብ ዓመቱን ለመቀየር አይችልም።
- ግብር ከፋዩ ቅድመ ሁኔታዎቹን ያጓደለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዘው ይችላል።
- የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት ሲቀየር በነባሩ የሂሳብ ዓመት እና በአዲሱ የሂሳብ ዓመት መካከል ያለው ጊዜ “የመሸጋገሪያ ዓመት” በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህ ጊዜ ራሱን እንደቻለ የሂሳብ ዓመት ይቆጠራል።
- የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት ከበጀት ዓመቱ ጋር የማይገጥም በሚሆንበት ጊዜ ለሂሳብ ዓመቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ህግ በሂሳብ ዓመቱ ውስጥ በሚጠናቀቀው የበጀት ዓመት ተፈፃሚ የሚሆነው ህግ ነው።

4.1. የሂሳብ አያያዝ ዘዴን ስለመለወጥ

- ግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን ለመለወጥ ባለሥልጣኑን በጽሁፍ ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን ባለሥልጣኑም ለውጡ የግብር ከፋዩን ገቢ በትክክል ለማስላት የሚያስፈልግ መሆኑን ሲያምንበት ግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን እንዲለውጥ በጽሁፍ ሊፈቅድለት ይችላል።
- የግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ በሚለወጥበት የግብር ዓመት የግብር ከፋዩ የግብር ከፋይ ደረጃም የሚለወጥ ከሆነ የግብር ከፋዩ ገቢ ሳይመዘገብ እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገብ ለማድረግ በገቢ ርዕሶች፣በተቀናሽ ወጪዎች ወይም በታክስ ማካካሻ ሂሳቦች ላይ የሒሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ያለበት፡-
    - የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፣

- በፈቃደኝነት የሒሳብ መዝገብ የሚይዝ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ እና
- የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ ጥቅም የሚያገኝ ሰው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለሲሆንከነዚህም በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ሠንጠረዥ ራሱን የቻለ የሒሳብመዝገብና መግለጫ መዘጋጀት ይኖርበታል።

4.2. የካፒታል ሀብት ሲተላለፍ የሚያዝቸ መረጃ

- የካፒታል ሀብት በማስተላለፍ ከሚገኝ ጥቅም ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ
  - የተላለፈው የካፒታል ሀብት የተገኘበትን ቀን፤የተገኘበትን ዋጋ፣
  - ሀብቱን ለማሻሻል የወጣ ማንኛውም ወጪእና
  - ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ለግብር ከፋዩ የተከፈለ የማስተላለፊያ ዋጋ አጠቃሎ የሚይዝ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት።
- የካፒታል ሃብት ማስተላለፍ የሚባለው፡-
  - ✓ የካፒታል ሀብትን በሽያጭ፤በስጦታ፤በዕርዳታ፤በአይነት መዋጮ መልክ ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ማት ነው።
  - ✓ የካፒታል ሃብት በአይነት መዋጮነት ሲተላለፍ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር የሚወሰን ባይሆንም የተላለፈው የካፒታል ሃብት ማስተላለፊያ ዋጋ የካፒታል ድርሻው ዋጋ ተደርጎ ይቆጠራል

4.3. ታክስ ከፋዩ መያዝ ያለበት ሰነድ ዓይነት

- ሂሳብ ነክ እና ሂሳብነክ ያልሆኑሰነዶች (ከመተዳደሪያደንብጀምሮ)
- የደረጃ ''ሀ'' ግብር ከፋይ የሒሳብ መዝገቡን የሚይዘው በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ(IFRS)አዋጅ መሠረት ሲሆን የኦዲት ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ ተግባራዊ እስከሚያደርግ ድረስ አጠቃላይ ተቀባይነት ያለውን የሒሳብ አያያዝ መርህ (Generally Accepted Accounting Principles) መሠረት በማድረግ የሂሳብ መዝገቡን ማዘጋጀት አለበት።

  ፣
- በዚህም መሰረት ግብርከፋይየሚይዘውየሂሳብመዝገብ
  - ማንኛውምየሂሳብመዝገብየሚይዝግብርከፋይየሚያከናውነውንእያንዳንዱንግብይትእንዲሁምየገንዘብናየንብረትገቢእናወጪየሚመዘግብበትየሒሳብመዝገብመያዝአለበት
  - ማንኛውምየደረጃ “ሀ” እናየደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ በግብር ከፋይነት ለተመዘገበበት እና የንግድ ፈቃድ ላወጣበት ለእያንዳንዱ የንግድ መስክ ያዋለውን ሀብት እና ኢንቨስትመንት እንዲሁም **በእያንዳንዱ ዘርፍ** ከተደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የተገኘውን ትርፍ እና ኪሣራ በትክክል የሚያሳይ በሀርድኮፒና ወይም በሶፍትኮፒ ተደራጅቶ የተያዘ ሰነድ መያዝ አለበት።
  - ግብር ከፋዩ ያለውን የንግድ ሥራሀብት(Fixed Assets) እንደዓይነቱ እና እንደአገልግሎቱ በመለየት የሚመዘግብበት የንግድ ሥራሀብት መዝገብ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የዚህ ዓይነት መዝገብ፡-

- ✓ እያንዳንዱ የንግድ ሥራሀብት የተገዛበት ወይም የተገኘበት ቀን እና ዋጋ፣
- ✓ የንግድ ሥራሀብቱን ለማሻሻል የተደረገ ማንኛውም ከሀያ በመቶ በላይ የሆነ ወጪ
- ✓ በዓመቱ መጨረሻ የንግድ ሥራሀብቱ ያለውን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ
- ✓ የእያንዳንዱ የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ መጠን የሚያሳይ መሆን አለበት።

- ➢ ኢንቨስትመንት የሚያካሂድ ግብር ከፋይ የኢንቨስትመንት ሥራው ተጠናቆ የኢንቨስትመንቱ አጠቃላይ ካፒታል እስኪታወቅ ድረስ በየጊዜው የሚወጣው ወጪ የሚመዘገብበት ራሱን የቻለ መዝገብ (ledger) ሊኖረውይገባል።
- ➢ ማንኛውም ግብር ከፋይ ብድር በሚወስድበት ጊዜ ወይም የዱቤ ግዥ በሚፈጽምበት ጊዜ የዕዳ መመዝገቢያ መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን መዝገቡ የሚከተሉትን አካቶ የያዘ መሆን አለበት፤
  - ✓ የብድር ወይም የዱቤ ሽያጭ ስምምነት፣
  - ✓ የዕዳ አከፋፈል ሁኔታ (Mode of payment)፣
  - ✓ የአበዳሪውዕቃ/ አገልግሎት በዱቤ የሸጠው ሰው ሙሉመረጃ፣
  - ✓ ነገርግን ግብር ከፋዩ የፋይናንስ ተቋም **ካልሆነ አካል** የሚበደረው ገንዘብ ከብር አምስትመቶበላይከሆነየብድርውሉበሚመለከተውአካልየተመዘገበመሆንአለበት።

- ➢ ማንኛውም ግብር ከፋይ የድርጅቱን ካፒታል የሚመዘግብበት የሂሳብ መዝገብ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን መዝገቡ የሚከተለውን መያዝ አለበት።
  - ✓ ካፒታሉ የግል ወይም በአክስዮን መዋጮ የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ፣
  - ✓ በአክሲዮን ድርሻ የተያዘው የካፒታል መጠን፣
  - ✓ የተከፈለ እና ያልተከፈለ የካፒታል መጠን፣
  - ✓ ያልተካፈፈለ የትርፍ መጠን፣
  - ✓ ለካፒታል ማሳደጊያ የዋለ የትርፍ መጠን፣
  - ✓ የተከፋፈለ የትርፍ ድርሻ መጠን

- ➢ ግብር ከፋዩ የግለሰብ ንግድ ድርጅት ከሆነ የባለቤቱ የግል ወጪ ራሱን ችሎ የሚመዘገብበት መዝገብ መያዝ አለበት።
  - ✓ ማንኛውም ግብር ከፋይ የድርጅቱን ጊዜያዊ ግዢ እና ሽያጭ የሚመዘግብበት የሂሳብ መዝገብ ሊኖረው ይገባል።
  - ✓ ማንኛ ውም ግብር ከፋይ ሽያጭ ወይምኮንስትራክሽን ወይም የምርት ስራውን ሲያከናወን ያወጣው የተለያየ አስተዳደራዊ ወጪ እና በዓመቱ መጨረሻ የሚደረግ የሂሳብ ማስተካከያ የሚመዘገብበት መዝገብ መያዝ አለበት።

- ✓ ግብር ከፋዩ ከዋናው የንግድ እንቅስቃሴ ውጪ የተገኘ ገቢ ወይም የወጣ ወጪ የሚመዘገብበት መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን በቻርት የተደገፈ የሒሳብ ዝርዝር አካውንትመግለጫ (chart of account) ሰነድ መያዝ አለበት።

4.4. የሒሳብ መግለጫ ይዘቶች

- ❑ በአጠቃላይ ግብር ከፋዩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሒሳብ መግለጫዎች ማዘጋጀት እና ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት
  - ➢ የሀብት እና የዕዳ መግለጫ (balance sheet) ፣
  - ➢ የጥሬ ገንዘብ ገቢ እና ወጪ መግለጫ (Cash flow statement)
  - ➢ የድርጅቱ የካፒታል ለውጥ መግለጫ (Change of capital statement) ፣
  - ➢ የትርፍ ና ኪሣራ መግለጫ (Profit and loss statement) ፣
  - ➢ አምራች ድርጅት ከሆነ የምርት ሂደት መግለጫ (Production statement) እና
  - ➢ ለተመረተምርትየወጣየምርትወጪመግለጫ (Statement of Cost of Goods Manufactured) እና Stock Inventory
- ❑ ታክስ ከፋዩ ንግድ ፈቃድ ያወጣበት የንግድመስክ ከአንድበላይ በሆነ ጊዜ ንዑስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Sub-TIN) ተጠቅሞ እያንዳንዱን የንግድ እንቅስቃሴ በተናጠል በተዘጋጀ የሂሳብ መዝገብ በመመዝገብ በዓመቱ መጨረሻ በዋናው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቃለለ የሒሳብ መግለጫ (consolidated financial statement) ማዘጋጀት አለበት።
  - ➢ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ቤት በማከራየት ወይም የንግድ ሥራ በማከናወን የተሰማራ ግለሰብ ግብር ከፋይ ለእያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር በተናጠል የተዘጋጀ የሒሳብ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

4.5. መረጃ እንዲቀርብ ስለሚሰጥ ማስታወቂያ

- ❑ የታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ አስተዳደር ወይም ለታክስ አወሳሰን የሚጠቅም ማንኛውን ም መረጃ እንዲያቀርብ ግብር ከፋዮን ወይም መረጃውን ይዞ የሚገኝ ማንኛውንም ሰው ሊያዝ ይችላል።
  - ➢ መረጃ እንዲቀርብለት የሚልከው ማስታወቂያ መረጃው የሚቀርብበትን ጊዜ እና የመረጃውን አይነት መግለጽ አለበት።
  - ➢ የታክስ ባለስልጣኑ መረጃ እንዲቀርብለት በሚልከው ማስታወቂያ የሚወስነው ጊዜ መረጃውን ለማደራጀት የሚያስፈልገውን ጊዜ እና መረጃው የሚገኝበት የቦታ እርቀት ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን መረጃውን ለማቅረብ የሚሰጠው ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ከ 10 ቀን ያነሰ መሆን የለበትም።
  - ➢ የታክስ ባለስልጣኑ ማንኛውንም ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ ወይም መረጃ እንዲያቀርብ ለተጠየቀው ሰው የሚያደርሰው በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 81 መሠረት መሆንአለበት።

- በህጉ በተደነገገው መሠረትማስታወቂያዉን ለግብር ከፋዩ ወይም መረጃ እንዲያቀርብ ለተጠየቀው ሰው ማድረስ ያልተቻለ እንደሆነ ማስታወቂያውን በግብርከፋዩ ወይም መረጃውን እንዲያቀርብ በተጠየቀው ሰው የንግድ አድራሻ ወይም መኖሪያቤት ግቢ ውስጥ ወይም በር ላይ በመለጠፍ ማስታወቂያው በትክክል መድረሱን ማረጋገጥ አለበት።

4.6. የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ግብር ከፋዩ ሶፍትዌር የሚጠቀም ከሆነ

ማንኛውም ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት ሶፍትዌር የሚጠቀም ከሆነ የሶፍትዌሩን ከአጠቃቀም ማንዋል ጋር ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

- ታክስ ባለስልጣኑ የሂሳብመዝገብ ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የሚውል ሶፍትዌር ሲቀርብለት ሶፍትዌሩ ለታክስ አስተዳደሩ አመቺ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
- ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ለማዘጋጀት በሚጠቀምበት ሶፍትዌር ላይለውጥ በሚያደርግበት ጊዜ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

4.7. ሂሳብ መዝገብ ባለመያዝ ከሚጣል መቀጫ ነጻ ስለመሆን/አለመሆን

- በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ የሚይዙ የደረጃ "ለ" ታክስ ከፋዮች የሒሳብ መዝገብ ሳይዙ በመቅረታቸው ወይም መዝገባቸው ተቀባይነት በማጣቱ ምክንያት መዝገብ ባለመያዝ የሚጣለው መቀጫ ተፈጻሚ አይሆንባቸውም።
- ሌሎች ተገቢ ሂሳብ መዝገብ ካልያዙ አስተዳደራዊ ቅጣትይቀጣሉ
- ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንደግለሰብ ታክስ ከፋይ ተቆጥረው ዓመታዊ ገቢያቸውን መሠረት በማድረግ በሚመደቡበት የግብር ደረጃ መሠረት የሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ ይደረጋል።

4.8. የግብር ከፋዩ ወጪተቀባይነት ስያጣ ማስተካከያዎች

- የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ማንኛውም ግብር ከፋይ ያቀረበው የወጪ ማስረጃ በታክስ ባለስልጣኑ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ውድቅ ሲደረግ ወጪው ገቢውን ለማመንጨት ወይም የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ወይም ለድርጅቱ ዋስትና ለመስጠት የወጣ ወጪ መሆኑ ሲረጋገጥ፡

  - ለቋሚ የንግድ ስራሀብት፣ዕቃው በተሰራበት ወይም በተገዛበት ወቅት የዕቃው የገበያ ዋጋ **70%**፣
  - ለሌሎች ዕቃዎች ግዢ፣የዕቃውን የገበያ ዋጋ **65%** በወጪነት በመያዝ ተቀናሽ ይደረጋል።
  - ነገርግን የቀረበው ወጪ ገቢውን ለማመንጨት ወይም የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ለድርጅቱ ዋስትና ለመስጠት የወጣ ወጪ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወጪው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ይደረጋል።
  - ግብር ከፋዩ የስራግብር በሚከፍልበት ጊዜ ያወጣው ወጪ የሚያዝለት ግብሩ ተቀናሽ የተደረገበት ተቀጣሪ ሙሉስም ና የሚከፈለውን የደመወዝ መጠን የያዘ ማስረጃ ሲያቀርብ ነው።
  - ቀጣሪው ለታክስ ባለስልጣኑ የሚያቀርበው የደመወዝ መክፈያ ሰነድ ክፍያው በባንክ ወይም በሶስተኛ ወገን የተከፈለ ካልሆነ በስተቀር በሰራተኛው የተፈረመበት መሆን አለበት።

4.9. ሰነድ በሚመለከተው አካል ስለማስመዘገብ

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የኪራይ ውሎች ሶስት ወር እና ከዚያ በላይ የሚቆዩ ከሆነ የውል ስምምነቱ በተፈረመበት ጊዜ በሚመለከተው አካል መመዝገብ አለበት።
  - ለንግድ ዓላማ የሚውል የቤት ኪራይ ፣የመጋዘን ኪራይ፤የጥናትአገልግሎት ግዢ፣ማንኛውም አይነት የማሽነሪ ኪራይ፣የንግድ ተሸከርካሪ ኪራይ፣
  - ይሁን እንጂ ሶስት ወር እና ከሶስት ወር በላይ የቆየ ወይም የሚቆይ የኪራይ ወይም የጥናት አገልግሎት ውል ስምምነት ያልተመዘገ በመሆኑ ከተረጋገጠ ሰነዱ ውድቅ ተደርጎ ወጪው በግምትይወሰናል።
  - የኪራይ ውሎች የተደረጉት ከመንግስት መስሪያቤቶች ጋር ከሆነ ውሉ መመዝገብ አያስፈልገውም።
  - ማንኛውም በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበ የውል ሰነድ በማስረጃነት በሚቀርብበት ጊዜ ሁለትእጥፍ የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልበት ይገባል።
  - ውሉን መሰረት አድርጎ የቀረበው ወጪ ገቢውን ለማመንጨት ወይም የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ለድርጅቱ ዋስትና ለመስጠት የወጣ ወጪ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወጪው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ይደረጋል።

4.10. የሂሳብ መዝገብ አዘገጃጀት

- የሂሳብ መዝገብ መያዝ ያለበት ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገቡ የሙያ ፈቃድ ባላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ወይም ሙያው እና የትምህርት ዝግጅቱ ባላቸው ተቀጣሪ የሂሳብ ሰራተኞች እንዲዘጋጅ ማድረግ ያለበት ሲሆን ግብር ከፋዩ አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት እና ሙያዊ ብቃትያለው ከሆነ የሂሳብ መዝገቡን ራሱ ሊያዘጋጅ ይችላል።
- የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ እናበፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ቀለል ያለ የሂሳብ ዘዴ በመጠቀም የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ።
- ግብር ከፋዩ የግንባታ ስራ የሚያከናውን ከሆነ ወጪው የሚመዘገበው ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያ እንደተፈጸመ ወጪዎቹ ተቀናሽ ይደረጉለታል።
  - ቀለል ያለ የሂሳብ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርብበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ አለበት።
    - ✓ ግብር ከፋዩ አስቀድሞ የተመዘገበውን የቋሚ የንግድ ስራሀብት ብዛት፣ዓይነት እና የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣
    - ✓ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተገዛ እና 100 % የእርጅና ቅናሽ የተደረገለት የንግድ ስራሀብት ብዛት፣ዓይነትናዋጋ፣
    - ✓ በግብር ዘመኑ የተላለፈ ወይም የተወገደ የንግድ ሥራሀብት ብዛት፣ዓይነት እና ዋጋ የሚገልጽ ደረሰኝና ተያያዥ ማስረጃዎች፤
    - ✓ ለቀጣይ የግብር ዘመን የዘረ ቋሚ ንብረት ብዛት፣ዓይነትእና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

- ✓ ካለፈው የግብር ዘመን ሳይሸጥ የቀረ ንግድ ዕቃ (Stock) ብዛት፣አይነት እና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፣

➢ ግብር ከፋዩ አምራች ከሆነ በግብር ዘመኑ በምርትሂደት ላይ ያለና ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ ጥሬ ዕቃ ብዛት፣አይነት እና ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፣

- ✓ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተፈፀመ የንግድ ዕቃ ሽያጭ እና ግዢ ዝርዝር ከግብይት ደረሰኝ ጋር፣
- ✓ በግብር ዓመቱ ውስጥ ለቤት ኪራይ የተከፈለ ወጪ እና ቤት በማከራየት የተገኘ ገቢመግለጫ፣ማቅረብ ይኖርበታል።

➢ ግብር ከፋዩ ግንባታ ስራ የሚያከናውን ከሆነ ወጪው የሚመዘገበው ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ ሲሆን የግንባታውን መጠናቀቅ የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት።

➢ ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው የሒሳብ መዝገብ መሰረታዊ ጉድለት ካልተገኘበት ና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያልያዘ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ውድቅ አይደረግም።

❑ ግብር ከፋዩ ያቀረበው የሂሳብ መዝገብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉድለቶች የተገኙበት እንደሆነ መዝገቡን ውድቅ ማድረግ ሳያስፈልግ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተደርጎ ግብሩ በመዝገቡ መሰረት ይወሰናል፤

➢ በሒሳብ መግለጫው ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተገለፀ ገቢ መኖሩ ሲረጋገጥ፤

➢ በደረሰኝ ላይ የተሰበሰበው ገቢ ድምር በሒሳብ መግለጫ ላይ ከሰፈረው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

➢ ግብር ከፋዩ ያስታወቀው የንግድሥራ ገቢ ከታክስ ነፃ የተደረገውን ግብይት ሳይጨምር ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ካስታወቀው ዓመታዊ ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት የተገኘበት ሲሆን፤እና

➢ በታክስ ከፋዩ የሒሳብ መግለጫ ላይ የተገለፀው ያልተሸጠ ዕቃ ዋጋ በቆጠራ ከተገኘው የዕቃ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ልዩነትያለው ሆኖ ሲገኝ።

❑ ግብር ከፋዩ ያቀረበው የሒሳብ መዝገብ በወጪ አመዘጋገብ ረገድ የሚከተሉት ጉድለቶች ሲገኙበት መዝገቡን **ውድቅ ማድረግ ሳያስፈልግ ማስተካከያ** (Adjustment) በማድረግ ግብሩ በመዝገቡ መሰረት ይወሰናል።

➢ ግብር ከፋዩ ባቀረበው ያልተመዘገበ ውል ላይ የተገለፀየ ንግድ ቤት እናየመጋዘንኪራይ፣የኮንስትራክሽን ማሽን ኪራይ፣የንግድ ተሸከርካሪ ኪራይ ወይም የረጅም ጊዜ ጥናት አገልግሎት ወጪ ሲገኝ፣

➢ ከፋይናንስ ተቋም ውጪ የተወሰደ እና ያልተመዘገበ የጥሬ ገንዘብ የብድር ስምምነት ሲቀርብ፣

➢ ተቀባይነት በሌለው ደረሰኝ ተገልጾ የቀረበወጪሲቀርብ፤

➢ በአዋጁ ያልተፈቀደ ወጪተይዞ ሲገኝ፤

➢ ግብር ከፋዩ ከፋይናንስ ተቋም ውጪ የወሰደው የጥሬ ገንዘብ ብድር ውል ስምምነት ውል የመስጠት ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ ከሆነ ብድር ነው ተብሎ በተገለፀው የገንዘብ መጠን ላይ ግብር ይወሰናል።

- ግብር ከፋዩ በገቢነት ያልገለጸው ሆኖ በግብር ከፋዩ ባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ከንግድ ስራ ያልተገኘ ወይም ግብር የማይከፈልበት ገቢስለ መሆኑ በተገቢው ህጋዊ ማስረጃ ማረጋገጥ ካልቻለ በተገለፀው የገንዘብ መጠን ላይ ግብርይወሰናል።

4.11. ግብር ከፋዩ ያቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችሉ ምክንያቶች

- የቀረበውን የሒሳብ መግለጫ ትክክለኛነት ግብር ከፋዩ ወይም የሂሳብ መግለጫውን ያዘጋጀው ባለሙያ በታክስ ባለስልጣኑ ሲጠየቅ በተገቢው ማስረጃ ያላረጋገጠ እንደሆነ፣
- ግብር ከፋዩ የሒሳብ መዝገብ እና ለግብር አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶችን እንዲያቀርብ በጽሁፍ ተጠይቆ ያላቀረበ እንደሆነ፣
- በደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ደረሰኝ ተጠቅሞ የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ ሲሆን፤
- ግብር ከፋዩ በታክስ ባለስልጣኑ ሲጠየቅ በተገቢው ማስረጃ ያላረጋገጠ ወይም ሰነዶችን እንዲያቀርብ በጽሁፍ ተጠይቆ ያላቀረበ እንደሆነ፣
- የሂሳብ መግለጫ ውድቅ የሚደረገው ኦዲተሩደጋፊ ሰነዶቹ እና የሂሳብ መግለጫው ማረጋገጫ በአስር ቀን ውስጥ ያልቀረበለት እንደሆነ ነው።
- ግብር ከፋዩ ያቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችሉ ምክንያቶች ተሟልተው የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ሲደረግ በኦዲት መውጫ ስብሰባ (exit conference) ጊዜ ለግብር ከፋዩ በጽሁፍ እንዲያውቀው የሚደረግ ሲሆን ግብርከፋዩ የሂሳብ መግለጫውንተቀባይነትያለውመሆኑንበቂሁኔታካላስረዳየታክስኦዲትውሳኔእንዲደርሰውይደረጋል።
- ግብር ከፋዩ ያቀረበው የሒሳብመግለጫ ተቀባይነት ያጣ እንደሆነ ታክሱበግምት የታክስ ስሌት መሠረት ይወሰናል።
- ነገር ግን የቀረበው የሂሳብ መግለጫ ውድቅ የተደረገበት ግብር ከፋይ መዝገብ ባለመያዝየሚ ጣለውቅጣትተፈፃሚ አይሆንበትም።

4.12. ስህተቶችን ስለማረም

- የታክስ ባለሥልጣኑ ግብርከፋዩ የሚያቀርበውን የሂሳብ መዝገብ መሠረት በማድረግ የታክስ ስሌት ሲወስን የሚከሰቱ ስህተቶችን ማረም የሚችለው በታክስህግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ የትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ የአጻጻፍ እና የሂሳብ ስሌት እንዲሁም ሌሎች የማያከራክሩ ስህተቶች ሆነው ሲገኙ ነው።
- ከላይ የተገለፀው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ባለስልጣኑ ከታች የተገለጹትን ስህተቶች በታክስ ስሌት አወሳሰን ሂደት የተከሰቱ እንደሆነ በራሱ አነሳሽነት ወይም ከግብር ከፋዩ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ስህተቱ በተፈፀመ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ማረምይችላል፤
  - የመደመር፤የመቀነስ፤የማባዛት እና የማከፈል ስህተት ሲያጋጥም
  - በስሌት ማጠቃለያ እና መንደርደሪያ መካከል የሚከሰት የስሌት ልዩነት(assessment inconsistency)
  - ከቁጥሮች በፊት ወይም በኋላ የቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ ወይም የቁጥር ቦታ መቀያየር(transposition)
  - የገቢ ወይም የወጪ ኮድ አመዘጋገብ ስህተት
  - የቃላት አገባብ ስህተት
  - በደረሰኝ ወይም በሌላ ማስረጃ የተመለከተ ሂሳብን ሳይደምሩ ወይም ሳይቀንሱ መተው ወይም መዝለል

- ከግብር ነጻ የሆነ ገቢን ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ መጨመር
- በአንድ ታክስ ከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሌላ ታክስ ከፋይ ሂሳብ መጨመር ወይም ማቀላቀል ወይም ማቀያየር
- የታክስ መጣኔ ወይም የትርፍ ህዳግ ማሳሳት
- ተቀባይነት ያለገኘ ደረሰኝ ላይ የተገለጸ ገንዘብ ስህተቱ የማይታረም ሲሆን ስህተቱ ሊታረም የሚችለው በተወሰነው የታክስ መጠን ላይ ታክስ በመጨመር ወይም በመቀነስ ሲሆን በተወሰነው የታክስ መጠን ላይ ለውጥ የማያመጣ ስህተት የሚታረመው ከግብር ከፋዩ ስም እና ማንነት ጋር የተያያዘ ሲሆን ብቻ ነው።

❑ **በሂሳብ መዝገብ የተወሰነ የታክስ ስሌት ላይ ስህተት ሲያጋጥም ከታች በተዘረዘሩት መንገዶች መሰረት የሚታረም ይሆናል**

- የታክስ ውሳኔ ላይ ስህተት አለበት የሚል ታክስ ከፋይ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በደረሰው 5 አመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ለሰጠው ቅ/ጽ/ቤት ጥያቄውን በጽሁፍ በማቅረብ ስህተቱ እንዲታረምለት ሊጠይቅ ይችላል።
- የታክስ ስሌቱን የሰራ ስራ ክፍል የታክስ ስሌት ማስታቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠ በኋላ በታክስ አዲት ሂደት የተፈጸመ ግልጽ እና የማያከራክር ስህተት ሲኖር ስህተቱን የፈጸመው ባለሞያ ወይም የሌላ ባለሞያ አስተያየት ቄምር በመያዝ ስህተቱ እንዲታረም በውሳኔ ሃሳብ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ያቀርባል።
- የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ስህተቱ የሚታረም ነው ወይስ የማይታረም የሚለውን ይወስናል ወሳኔው በዚህ የማይቋቄ ከሆነ የታክስ ህጉን ተከትሎ ጉዳዩ እስከ ሚኒስትሩ ይቀጥላል።ሚኒስትሩም የሚሠጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

4.13. በማስታወቂያ መረጃ ወይም ማስረጃ መጠየቅ

❑ ባለሥልጣኑ የታክስ ህጐችን በማስተዳደር ግብር/ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው ሰነድ የሚቀርብበትን ቦታ፣ጊዜና የሰነዱን ዓይነት የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ማንኛውም ዓይነትመረጃ እንዲሰጠው ወይም እንዲቀርብለት መጠየቅ የሚችልመሆኑ፣

❑ በባለሥልጣኑየሚጠየቀው መረጃ የኤሌክትሮኒክስ መረጃን ጨምሮ በማስታወቂያው የተጠቀሰው መረጃ ሌላ ልዩ መብት የሚያሰጥ ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከት ወይም ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል ወይም ስምምነት ቢኖርም መረጃው መሰጠት እንደሚኖርበት፣

❑ ለባለሥልጣኑ የተሰጠው ሥልጣን ልዩ መብት በሚያሰጡ የህግ ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም በሚመለከቱ ገደቦች ና ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታን በሚጥሉ ውሎች ወይም ስምምነቶች የማይገደብ መሆኑ፣

4.14. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን

❑ ማንኛውንም የታክስ ህግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ፣

- ያለማስታወቂያ በማንኛውምጊዜ፣በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ ገብቶ ማንኛውንም ዕቃ ወይም ንብረት የመበርበርና የመያዝ/ወስዶ ለታክስ ህጉ አፈጻጸም የመጠቀም፣
- ማንኛውንም ሰነድ ወይም የመረጃ ማከማቻ ቅጂ ወይም ዋናውን የመያዝና ወስዶ ለታክስ ህጉ አፈጻጸም የመጠቀም፣
- ማንኛውንም ለታክስ አወሳሰን የሚጠቅም መረጃ የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታለመወሰንወይምለማንኛውምየታክስክርክርእስካስፈለገበትጊዜድረስይዞማቆየትይችላል።

- መተባበር ግዴታን አለመወጣት ግለሰቡን ወይም ድርጅት ከሆነ ኃላፊው በብር 5000 የገንዘብ መቀጫ ያስቀጣል።
- ሲጠቃለል ለባለሥልጣኑ በአዋጅ የተሰጠው፣
  - ✓ መረጃን የመጠየቅ፣
  - ✓ ሰነድን የመመርመር፣
  - ✓ ቤትና ቦታን ወይም ይዘታን የመበርበር፣
  - ✓ ሰነድን ወይም መረጃን የመያዝ ወይም ወስዶ ለታክስ አስተዳደር ዓላማ የመጠቀም ሥልጣን የህዝብና የግል ጥቅምን እንዲሁም የግል (Privacy) መብትን ለማስከበር በወጡ ህጎች ወይም ሚስጥራዊነትን ለማስጠበቅ በተደረጉ የውል ስምምነቶች አይታገድም።

4.15. ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች

- ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ከተዋዋለው የረዥም ጊዜ ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሠረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ሲያካትት ወጪውም በዚያው መቶኛ ልክ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል።
- በግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገው ውል ውስጥ በግብር ዓመቱየተጠናቀቀው በመቶኛ የሚወሰነው በግብር ዓመቱ የሚኖረውን ለውጥ ጨምሮ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ያወጣውን ወጪ ከአጠቃላይ የውሉ ወጪ ግምት ጋር በማነፃፀር ይሆናል።
- ግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ በውሉ የመጨረሻ ዓመት ኪሳራ የደረሰበት ከሆነ ኪሳራውን እንዲያሸጋግር የተፈቀደለት ቢሆንም ኪሳራውን ማሸጋገር ያልቻለ ሆኖ በውሉ ዘመን መጨረሻ በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ መሥራት ያቆመ እንደሆነ ይህ ግብር ከፋይ የደረሰበት ኪሳራ ወደ ኋላ ተመልሶ በአምናው የግብር ዓመት በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል።
- ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሳራወደ ኋላ ተመልሶ ሙሉ በሙሉ በተቀናሽ ወጪነት እንዲያዝ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣ ያልተቀነሰው ኪሳራ ወደኋላ ተመልሶ ወደ አቻምናው የግብር ዓመት የሚሸጋገር ሆኖ ተቀናሽ ይደረጋል።
- ግብር ከፋዩ በረዥም ጊዜ ውል ኪሣራ ደርሶበታል የሚባለው የሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፦
  - ሀ)የተጠናቀቀውን ሥራ በመቶኛ ለማስላት ዘዴ ዓላማ ሲባል በውሉ ይገኛል ተብሎ

የተገመተው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በእርግጠኛነት ከተገኘው ግብር ከሚከፍለበት ገቢ

በልጦ ሲገኝ፤ እና

- ለ)በፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በብልጫ የታየው ገንዘብ ተሰልቶ ከተደረሰበት ውሉ በተጠናቀቀበት የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢና ወጪው መካከል ካለው ልዩነት በልጦ ሲገኝ፤
- ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል ማለት፦ ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ 12 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዓመት ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው።

የመከራየቄ ስድስት

1 ኛ. ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ ግብር ከፋዩ ኪሳራ ቢያጋጥመው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው በምን መልኩ ነው? አብራሩ

2 ኛ. ግብር ከፋዩ በሚያቀርበው የሂሳብ መዝገብ ላይ ስህተቶች ሲያጋጥሙ በባለስልጣኑ እንዴት ይታረማሉ? ዘርዝሩ

ክፍል አምስት

5. ድርጅትን በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥና የኩባንያ እንደገና መደራጀት

5.1. አንድን ድርጅት በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥ (34)

- አንድ ድርጅት የደረሰበትን ኪሣራ ወደ መሸጋገሪያ ዓመት ወይም ወደ ሚቀጥለው ዓመት ማሸጋገር የሚችለው የኩባንያውን ከ 50% በላይ የሆነውን የዋና ባለቤትነት ድርሻ በኪሣራው ዓመት ፣ በመሸጋገሪያው ዓመትና በሁሉም ጣልቃ ገብ ዓመታት የያዘው ተመሳሳይ ሰው የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው።ሆኖም ግን ፡-
- ድርጅቱ በኪሣራው ዓመት፣ በመሸጋገሪያው ዓመትና በሁሉም ጣልቃ ገብ ዓመታት አንድ ዓይነት የንግድ ስራ እየሰራ ያለ ከሆነ፣
- የዋና ባለቤትነት ለውጥ ከተደረገም በኋላ ድርጅቱ በሌላ የንግድ ስራ የተሰማራው ኪሣራውን ከአዲሱ ስራ ገቢ ላይ ለማካካስና ገቢውን ለማሳነስ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ኪሣራውን እንዳያሸጋግር አይከለከልም።

5.2. የኩባንያ እንደገና መደራጀት

- እንደገና መደራጀት **(reorganization)**ማለት፡-
  - ከሁለት በላይ የሆኑ ነዋሪ ኩባንያዎች መዋሃድ።
  - የአዲሱ ድርጅት አባል የሆነ አንድ ድርጅት የሌላውን ድርጅት 50% ልዩ የአክሲዮን ባለቤት ድርሻ ከአዲሱ ድርጅት በሚገኘው የአክሲዮን ለውጥ ብቻ መያዝ።
  - እንደገና በሚደራጀው ድርጅት ውስጥ አባል የሆኑ ሁለት ድርጅቶች አንዱ የሌላውን ከ 50% በላይ የሆነ የአክሲዮን ባለቤትነት ድርሻ ልዩ መብት በማያሰጥና የድምጽ ተሳትፎ ብቻ በሚያስገኝ አኳኋን መጠቅለል።
  - የአንድ ድርጀት ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደ ሆኑ ኩባንያዎች መከፋፈል።
  - የአንድ ድርጅት የተቀጽላዎችን ካፒታል የድርጅቱን ካፒታል ለያዘ ሌላ ድርጅት ማስተላፍ።አንድ ኩባንያ እንደገና ከመደራጀት ጋር ተያይዞ ለሌላ ኩባንያ የንግድ ስራ ሃብት በሚያስተላልፍበት ጊዜ የንግድ ስራ ሃብቱ እንደተሸጠ፣ እንደተለወጠ ወይም እንደተሰጠ (እንደተላለፈ) አይቆጠርም።
  - የንግድ ስራ ሃብቱን ያገኘው ድርጅት አስተላላፊው የንግድ ስራ ሃብቱን ለማግኘት ከወጣው ወጪ ጋር እኩል የሆነ ወጪ በማውጣት እንዳገኘው ይቆጠራል (transferred at Book value)።
  - የንግድ ስራ ሃብቱ የተላላፈለት ሰው በምትኩ አክሲዮን የሰጠ እንደሆነ በአክሲዮኖቹ የተደረገው ወጪ የተላለፈው ሃብት በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።
  - ለንግድ ስራው ሃብት የተደረገው ወጪ የሚለው የንግድ ስራ ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረውን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚመለከት ነው።

- በእንደገና መደራጀት ሂደት የተላለፈ የንግድ ስራ ሃብት እንደተላለፈ የማይቆጠረው የእንደገና መደራጀቱ ዓላማ ከታክስ ለመሸሽ ያለመሆኑ በባለስልጣኑ ሲታመንበት ነው።

5.3. የማዕድንና የነዳጅ ስራዎች ገቢ ግብር

5.3.1. የማዕድንና የነዳጅ ስራዎች ልዩ ባህሪ

- የማዕድንና የነዳጅ ስራ ከሌላው የንግድ ስራ ለየት የሚያደርገው፦
  - የገቢ ምንጩ ሊተካ የማይችል የመንግስት (የሃገር) የተፈጥሮ ሃብትን በመጠቀም የሚገኝ በመሆኑ።
  - ስራው ከፍተኛ ስጋት (Risk) ያለበትና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ።
  - የማዕድንና የነዳጅ ፈለጋ ስራ ረጅም ጊዜ የሚወስድና በስተመጨረሻም ውጤት እንደሚገኝ አስቀድሞ እርግጠኛ መሆን የማይቻልበት ሁኔታ (uncertainity) ያለበት በመሆኑ።
  - ንግዱ የመንግስት ልዩ ፈቃድ የሚጠይቅና ልዩ ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት እንዲሁም የመንግስት ድርሻ ያለበት በመሆኑ።
  - ንግዱ የመንግስትን ልዩ መብት (Royal interest of the state) የሚጋራና ከፍተኛ የመንግስት ጥቅም ያለበት በመሆኑ ወዘተ ነው።

5.3.2. ፈቃድ በተሰጠው ሰውና በስራ ተቋራጭ ላይ ግብር ስለመጣል

- ማዕድን የማውጣት መብት በተሰጠው ባለፈቃድ (ፈቃድ የተሰጠው ሰው) እና ከመንግስት ጋር የነዳጅ ስምምነት ባደረገው ስራ ተቋራጭ ላይ የተጣለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር 25% ነው።
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ከሚፈጽመው ማንኛውም ክፍያ ላይ የሞቢላይዜሽንና የዲሞቢላይዜሽን ወጪዎች ተቀንሰው በሚቀረው መጠን ላይ 10% ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት። የነዳጅ ንዑስ ስራ ተቋራጭ ከዚህ ዓይነት ግብር ነጻ ተደርጓል።
- ስለማዕድንና ነዳጅ ስራዎች ገቢ የሚደነግገው የአዋጁ ክፍል ከሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ቢጋጭ ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ስለማዕድንና ስለነዳጅ ስራዎች የሚደነግጉት የአዋጁ ክፍሎች ናቸው። ከዚህ ክፍል ጋር የማይቃረኑ ሌሎች የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ግን ከማዕድንና ነዳጅ ስራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

5.3.3. በማዕድን ወይም በነዳጅ ስራዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎችን ስለመገደብ

- ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ተቀናሽ የሚደረግላቸው ወጪ፣
  - ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ፈቃድ በተሰጠበት አካባቢ ወይም የውል ክልል ውስጥ በግብር ዓመቱ ካገኙት የንግድ ስራ ገቢ ላይ የዓመቱን ወጪ ተቀናሽ ማድረግ ይችላሉ።
  - ኪሳራ ያጋጠማቸው እንደሆነ ኪሳራው ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ተሸጋግሮ ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ወይም በውሉ ክልል የማዕድን ወይም የነዳጅ ስራ በመስራት ከሚያገኙት የንግድ ስራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።
  - ኪሳራ ለማሸጋገር የሚቻለው ኪሳረው ከደረሰበት አመት ቀጥሎ ላሉት አስር አመታት ነው።
  - ባለፈቃዱና ስራ ተቋራጩ ኪሳራ ደረሰባቸው የሚባለው በግብር ዓመቱ ካገኙት ጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ የግብር ዓመቱ ጠቅላላ ወጪ የበለጠ እንደሆነ ነው።

➢ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱና ስራ ተቋራጩ የሚከተሉት ተቀናሾች ይፈቀዱላቸዋል።

1. የፍለጋ ወጪዎች

➢ የፍለጋ ወጪ ማለት ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች የሚወጣውን ወጪ ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩየምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚወጣ ወጪሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

- ✓ ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋን መብት የሚመለከት ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም
- ✓ ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋ መረጃን ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም
- ✓ ከማዕድን ፍለጋ ሥራ ወይም ከነዳጅስምምነት ጋር ተያይዞ ለማህበራዊ መሠረተ ልማት ግንባታ የሚወጣ ወጪ፤
  - የአገልግሎት ዘመናቸው አንድ ዓመት የሆኑ የፍለጋ ወጪዎች ግዙፋዊ ህልወት የሌላቸው የንግድ ስራ ሃብቶች ተደርገው ይወሰዳሉ።
  - ለመጀመሪያ ጊዜ ለፍለጋ ስራ ጥቅም ላይ የዋለ የንግድ ስራ ሃብት የእርጅና ቀናሽ መጣኔው 100% ይሆናል።

2. የማልሚያ ወጪ፣

➢ የማልሚያ ወጪ.ማለት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የሚወጣን ወጪ ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት የሚወጣ የካፒታል ወጪሲሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል።

- ✓ የፍለጋ ወጪ ለሚለው ሀረግ በማዕድን ማውጣት ወይም በነዳጅ ሥራ ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም
- ✓ የማዕድን ማውጣት ወይም የነዳጅሥራ መረጃ ለማግኘት የወጣ ወጪ፤
- ✓ ከማዕድን ማውጣት መብት ወይም ከነዳጅ ስምምነት ጋር በተያያዘ ለማህበራዊ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ የሚወጣ ወጪ፣
  - የማልሚያ ወጪ ለአራት ዓመታት ያህል የሚያገለግል ግዙፋዊ ህልወት የሌለው የንግድ ስራ ሃብት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።
  - ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት የወጣ የማልሚያ ወጪ ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት ጊዜ እንደወጣ ወጪ ተቆጥሮ የእርጅና ቅናሽ ይታሰብለታል።
  - ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ለማልሚያ ስራዎች አገልግሎት የሚውል ዋጋው የሚቀንስ የንግድ ስራ ሃብት የተገዛ ወይም የተገነባ እንደሆነ ሃብቱ ለንግድ ስራ የሚሆን ምርት በተጀመረበት ጊዜ እንደተገዛ ወይም እንደተገነባ ተቆጥሮ የእርጅና ቀናሽ ይታሰብለታል።
  - ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት ተጀምሯል የሚባልበት ጊዜ የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር በሚወስነው መሠረት ከ 30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከፍተኛ ምርት ማምረት በተቻለባቸው 25 ቀናት ካሉት 30 ቀናት ውስጥ የመጀመሪያው ቀን ነው።
  - የሚፈቀደው የማልሚያ ወጪ ተቀናሽ መጠን ወይም በእርጅና ምክንያት ዋጋው ለሚቀንስ የንግድ ሥራ ሀብት በግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡-ሀ × $\frac{ለ}{ሐ}$

ሀ)የወጪው መጠን ወይም ለሀብቱ የተደረገ ወጪ፣

ለ)ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ለንግድ ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት የመጨረሻ ቀን መካከል ያሉት ቀናት፣

ሐ)ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት ያሉትቀናት ብዛት፣

ከማዕድን ስራ መብት ወይም ከነዳጅ ስምምነት ከተገኘ መብት አንድ መብት የተላለፈ እንደሆነ መብቱን በማስተላለፍ የተገኘው ጥቅም ተደርጎ የሚወሰደው ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ያልመለሰውን ሂሳብ ሳይጨምር የማስተላለፍ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ተቀናሽ የተደረገላቸው የማልሚያ ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ዋጋ ነው።

3. የመልሶ ማቋቋሚያ ወጪ፣

- በመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሰረት ለመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ የሚደረገው መዋጮ መዋጮው በተደረገበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዛል።
  - ✓ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድማለት ፈቃድ የተሰጠበትን ክልል ወይም የውል ክልል መልሶ ለማስተካከል የሚውል በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር እና በባለፈቃዱ ወይም በስራ ተቋራጩ በጋራ የሚተዳደር ገንዘብ ነው።
  - ✓ ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ ተደርጎ ያልተተካ በፀደቀ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት ለተሰራ ሥራ የወጣ ወጪ ወጪው በወጣበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዛል።
  - ✓ በመልሶ ማቋቋም ስራ ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ የሚደረግ የገንዘብ መጠን ከግብር ነጻ ነው።
  - ✓ ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ ተደርጎ ለባለፈቃዱ ወይም ለስራ ተቋራጩ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠን ገንዘቡ ተመላሽ በተደረገበት የግብር ዓመት እንደ ንግድ ስራ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል።

4. የኢንቨስትመንት ተቀናሽ

- በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በተፈቀዱ ሌሎች የልማት መስኮች ኢንቨስት ለሚደረግ የኢንቨስትመንት ወጪ ከእያንዳንዱ የግብር ዓመት ጠቅላላ ገቢ ላይ እስከ 5% ተቀናሽ ይፈቀዳል፤ይህ የኢንቨስትመንት ገንዘብ ተቀናሽ ከተደረገበት የግብር ዓመት ቀጥሎ እስካለው የግብር ዓመት መጨረሻ ድረስ ኢንቨስት ካልተደረገ በዚሁ የግብር ዓመት ጠቅላላ ገቢ ላይ ይደመራል።

5.3.4. የማዕድን ወይም የነዳጅ መብት ስለማስተላለፍ

- የማዕድን ወይም የነዳጅ መብትን ማስተላለፍ የሚቻል ቢሆንም መብቱ ሲተላለፍ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው።
  - ➢ ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ መብቱ ከሚተላለፍበት ሰው ጋርየማስተላለፍ ስምምነትተብሎ የሚጠቀስ የጹሁፍ ስምምነት ማድረግ አለባቸው።
  - ➢ ለሚተላለፈው መብት የሚከፈለው ዋጋ፣
    - ✓ መብት የተላለፈለት ሰው ሊከፍል የተስማማበትን ወጪ እና
    - ✓ ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ካስቀረው የተወሰነ መብት የሚመነጩ ግዴታዎችን መብቱ የተላፈለት ሰው መብት አስተላላፊውን ተክቶ ለመውጣት የሚገባውን ግዴታ ለመፈጸም የሚያወጣውን ወጪ የሚጨምር መሆን አለበት።

- የማዕድንና የነዳጅ መብትን ማስተላለፍ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፡-
  - መብት አስተላላፊው ካስቀረው መብት ጋር በተያያዘ መብት የተላለፈለት ሰው በራሱ የሚያከናወነው ስራ ዋጋ መብት አስተላላፊው ለተላለፈው መበት በተቀበለው ዋጋ ውስጥ ወይም በመብት አስተላላፊው የንግድ ስራ ገቢ ውስጥ አይካተትም።
  - መብት አስተላላፊው ከተላለፈው መብት ጋር በተያያዘ ላወጣው ወጪ ያገኘው ተቀናሽ ተመላሽ እንደተደረገ ወጪ ተቆጥሮ በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ገቢ ተርጎ ይወሰዳል።
  - ተቀናሽ ወጪው መብት አስተላላፊው ከተቀበለው የገንዘብ መጠን የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የታየው ገንዘብ የተላለፈው መብት ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

5.3.5. የማዕድን ወይም የነዳጅ መብትን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለማስተላለፍ

- የባለፈቃዱ ወይም የስራ ተቋራጩ ድርጅት ዋና ባለቤትነት ከ 10% በላይ ከተለወጠ ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ ለውጡን ለባለስልጣኑ ወዲያወኑ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።
- ከላይ የተገለጸውን ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ ያለበት የመብት አስተላላፊ የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ ባለፈቃዱ ወይም ስራ ተቋራጩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው የመብት አስተላላፊ ወኪል እንደሆነ ተቆጥሮ ከመብት ማስተላለፉ ጋር ተያይዞ በ አዋጁ መሰረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።
- ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በባለፈቃዱ ወይም በስራ ተቋራጩ የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነውን የመብት አስተላላፊ በመወከል የተከፈለ ማንኛውም ግብር ከመብት አስተላላፊው (ነዋሪ ካልሆነው ሰው) ላይ ከሚፈለገው የታክስ ዕዳ ጋር ይካካሳል።
- በማዕድን ወይም በነዳጅ ስራ በተሰማራ አንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የአባልነት ጥቅም እንደንግድ ስራ ሃብት ተደርጎ ይወሰዳል።

5.4. ዓለም አቀፍ ግብር

5.4.1. በውጭ አገር የተከፈለን የንግድ ስራ ገቢ ስለማካካስ

- በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በውጭ አገር ካገኘው የንግድ ስራ ገቢ ላይ የውጭ አገር ግብር የከፈለ እንደሆነ በውጭ አገር የከፈለው የንግድ ስራ ገቢ ግብር እንዲካካስለት ይደረጋል። የሚካካሰው የግብር መጠንም ፡-
  - በውጭ አገር ከተከፈለው ገቢ ግብር ፣
  - በውጭ አገር በተገኘው ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ስራ ገቢ ግብር
  - ከሁለቱ ከአነስተኛው የበለጠ አይሆንም።
  - ከውጭ አገር በተገኘው ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባው የንግድ ስራ ገቢ ግብር የሚሰላው በግብር ከፋዩ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነውን አማካይ የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ ግብር ከፋዩ ባገኘው የተጣራ የውጭ አገር ገቢ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ነው።
  - አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ ማለት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው የግብር ዓመቱ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተግባራዊ የሚሆነው የግብር መጣኔ ነው፤

    በውጭ አገር የተከፈለ ግብር ሊካካስ የሚችለው፣
    - ✓ ግብር ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውን ግብር ገቢው ከተገኘበት የግብር ዓመት ቀጥሎ ባሉት ሁለት የግብር ዓመታት ወይም ደግሞ ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የከፈለ እንደሆነና
    - ✓ ግብር ከፋዩ በውጭ አገር ለከፈለው ግብር ከውጭ አገር የታክስ ባለስልጣን የተሰጠ ደረሰኝ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው።

- ✓ በውጭ አገር ለተከፈለ ግብር የተፈቀደ ማካካሻ ከሌሎች ማናቸውም የግብር ማካካሻዎች አስቀድሞ ተግባራዊ መደረግ አለበት።
- ✓ በአንድ የግብር ዓመት ተካክሶ ያላለቀ የውጭ አገር ግብር ወደ ሌሎች የግብር ዓመታት አይሸጋገርም ።(Loss cary forward or Loss cary back ward አይፈቀድም።)
- ✓ የተጣራ የውጭ አገር ገቢ ነው የሚባለው፣ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ግብር ከፋዩ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ አገር ገቢ ላይ ፡-
- ✓ የውጭ አገር ገቢውን ለማግኘት ሲባል ብቻ የተደረገ ወጪ።
- ✓ የውጥ አገር ገቢ ራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚመደብ በመሆኑ የውጭ አገር ገቢውን ለማግኘት በወጣው መጠን ተከፋፍሎ የተመደበ ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ገቢ ነው።

5.4.2. የውጭ አገር የንግድ ስራ ኪሳራዎች

- ❑ ግብር ከፋዩ የውጭ አገር ገቢን ለማግኘት ያወጣው ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው በውጭ አገር ካገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው።
- ❑ በግብር ዓመቱ በውጭ አገር ያጋጠመውን ኪሳራ ግብር ከፋዩ በሚቀጥለው የግብር ዓመት ከውጭ አገር ባገኘው ገቢ ላይ በማካካስ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ተቀናሽ ይደረግለታል።
- ❑ በሚቀጥለው የግብር ዓመት ተቀናንሶ ያላለቀ ኪሳራ እስከሚቀጥሉት አምስት የግብር ዓመታት ድረስ ሊሸጋገርና ሊቀናነስ ይችላል። ሆኖም ኪሳራው ከደረሰበት የግብር አመት በኋላ ካሉት አምስት ዓመታት በላይ ኪሳራውን ለማሸጋገር አይቻልም።
- ❑ ወደሚቀጥሉት የግብር ዓመታት ማሸጋገር የሚቻለው የሁለት ግብር ዓመታት ኪሳራ ብቻ ነው።
- ❑ በውጭ አገር የደረሰ ኪሳራ የሚባለው በሰነጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት የውጭ አገር ገቢ ለማግኘት ግብር ከፋዩ ያወጣቸው ወጪዎች መጠን ከጠቅላላው የውጭ አገር ገቢ በልጦ ሲገኝ ነው።

5.4.3. ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር (Thin capitalization)

- ❑ በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ከአማካይ የካፒታል መዋጮው ጋር ሲነጻጸር ከ 2 ለ 1 ሬሽዮ የበለጠ እንደሆነ ኩባንያው ከዚህ ሬሽዮ በላይ በሆነው ዕዳ የከፈለው ወለድ አይቀነስለትም።
- ❑ ተቀናሽ የማይደረገው የወለድ መጠን ቀጥሎ በተመለከተው ስሌት መሰረት ይወሰናል፡-

$$ሀ \times \frac{ለ}{ሐ}$$

➢ በዚህስሌት ፡-

- ➢ ሀ) ኩባንያው በግብር ዓመቱ ተቀናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የወለድ ወጪ፤
- ➢ ለ) ኩባንያው ከተፈቀደው መጠን በላይ የወሰደው ብድር፤ እና
- ➢ ሐ) ኩባንያው በግብር ዓመቱ ያለበት አማካይ ዕዳ ነው።

- የካፒታል መዋጮ ማለት፡- በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ የወለድ ክፍያን የማይጨምር ዕዳን መልሶ የመክፈልን ግዴታ የሚያስከትል ብድርን ጨምሮ በሂሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት በግብር ዓመቱ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛው የኩባንያው የካፒታል መዋጮ ነው።
- አማካይ የካፒታል መዋጮ ማለት፣ በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተከፈለ በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን የካፒታል መዋጮ ነው። $\frac{ሀ}{12}$
- ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ሀ) በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ለኩባንያውየተደረገ

ጠቅላላ የካፒታል መዋጮ መጠን ነው።

- ዕዳ ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በሚወሰነው መሠረት ወለድ የሚከፈልበት የኩባንያው ዕዳ የመክፈል ግዴታ ነው።
- አማካይ ዕዳ ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያበሚመለከት በግብር ዓመቱ ውስጥ የወሰደው በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን ዕዳ ነው። $ሀ/_{12}$
- ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ሀ - በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ኩባንያውየሚፈለግበት

ጠቅላላ የዕዳ መጠን ነው።

- ዕዳ የመክፈል ግዴታ ማለት ከቃል ኪዳን ሰነድ፣ ከሀዋላ፣ እና ከቦንድ የሚመጣን ግዴታ ጨምሮ ለሌላ ሰው ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ ነው።የሚከተሉትን ግን አይጨምርም
  - ✓ ተከፋይ ሂሳቦችን፤ ወይም
  - ✓ ወለድ የመክፈል ግዴታን የማያስከትል ማናቸውንም ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ፤
- በብልጫ የታየ ዕዳ ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ ኩባንያው ያለበት አማካይ ዕዳ በ2ለ1 ቀመር መሠረት ከተፈቀደለት ከፍተኛው አማካይ ዕዳ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠንነው።
- ሆኖም በውጭ ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለው በኢትዮጵያዊ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ አማካይ ዕዳ እና አማካይ የካፒታል መዋጮ ከ2ለ1 ሬሽዮ ቢበልጥም የኩባንያው የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ከተወሰደው ዕዳ የማይበልጥ ከሆነ ከላይ የተመለከተው ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም።
- ከላይ የተጠቀሱት በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ባለው የኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።
- ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ፡-
  - ✓ ድርጅቱ በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር እንዳለ ኩባንያ ሆኖ ይቆጠራል።
- የድርጅት አማካይ ዕዳና አማካይ የካፒታል መዋጮ የሚሰላው፡-

- ✓ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በቋሚነት ለሚሰራ ድርጅት ለማዋል የወሰደው ብድር፣ እና
- ✓ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ በቋሚነት ለሚሰራው ድርጅት መንቀሳቀሻ የመደበው ወይም ያዋለው የካፒታል መዋጮ ከግምት ውስጥ ገብቶ ነው።
- ✓ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች የተወሰደ ዕዳ ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ኩባንያ በሚመለከት አንድ የፋይናንስ ተቋም ኩባንያው የሚገኝበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት ዓይነት ሊያበድረው የሚችል ገንዘብ ነው።

5.4.4. ግብርን በሚመለከት የሚደረጉ ስምምነቶች (tax treaties)

- ❑ የግብር ስምምነት ማለት፡-0 ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረትና ታክስ ላለመክፈል የሚደረግን የግብር ስወራ (Tax Evasion) ለመከላከል የሚደረግ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው።
- ❑ ግብርን የሚመለከቱ ስምምነቶች ከውጭ አገር መንግስት ወይም መንግስታት ጋር የሚደረጉት በገ/ኢ/ት/ሚ/ ነው።

❑ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚነት ባለው የግብር ስምምነት የውል ቃላትና በዚህ አዋጅ መካከል አለመጣጣም የተፈጠረ እንደሆነ የስምምነቱ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

❑ ይሁንና አለመጣጣሙ የተፈጠረው ፡-

- ➢ በተዋዋይ አገር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ከ 50% በላይ ባለቤት የሆነበት ድርጅት የታክስ ነጻ መብትን በሚያሰጥና የግብር ማስከፈያ መጣኔ ቅነሳን በሚያስከትል የግብር ስምምነት ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል ፣ እና
- ➢ ከግብር ለመሸሽ የሚደረግን ጥረት ስለመከላከል ከተቀመጡት የአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር ከሆነ የስምምነቱ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም

❑ በተዋዋይ አገር ነዋሪ ባልሆነና ከ 50% በላይ የአክሲዮን ባለቤትነት ባለው ሰው ቁጥጥር ስር ያለ ድርጅት ቢሆንም የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በታክስ ስምምነቱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

- ➢ የተዋዋይ አገር ነዋሪ ባልሆነ ሰው ከ 50% በላይ በባለቤትነት የተያዘው ድርጅት በተዋዋዩ አገር የአክሲዮን ገበያ ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ኩባንያ ከሆነ ወይም፣
- ➢ በተዋዋዩ አገር በሚገባ የሚንቀሳቀስ የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ እንደሆነና በኢትዮጵያ ለተገኘው ገቢ ምንጭ የሆነው ይኸው የንግድ ስራ የሆነ እንደሆነ።

❑ በሚገባ የሚንቀሳቀስ የንግድ ስራ የሚለው ቃል ኩባንያው የገንዘብ ተቋም ወይም የኢንሹራንስ ኩባንያ ካልሆነ በስተቀር የአክሲዮን፣ የዋስትና ሰነዶች ወይም የሌሎች ኢንቨስትመንቶች ባለቤት መሆንን ወይም ማስተዳደርን አይጨምርም።

5.5. የወል ድንጋጌዎች

❑ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት የወል (common) ድንጋጌዎች ለሁሉም የግብር ሰንጠረዦችና የግብር ዓይነቶች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

1. ሃብት ስለማግኘት

- ✓ አንድ ሰው ሃብት አገኘ የሚባለው የሃብቱ ባለቤትነት ስም (ownershiptittle) ከተላለፈለት ጊዜ ጀምሮ ነው።
- ✓ ሃብቱ መብት ወይም ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ ሃብቱ ተላለፈ የሚባለው መብቱ ወይም ምርጫው የተሰጠበት ጊዜ ነው።

2. ሃብትንስለማስተላለፍ

- ✓ አንድ ሰው ሃብቱን አስተላለፈ የሚባለው ሃብቱን ሲሸጥ ፣ ሲለውጥ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ በሃብቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ሲያስተላልፍ ነው።
- ✓ በተጨማሪም፦
- ✓ በሃብቱ ላይ ያለው ባለቤትነት ከመዘገብ እንዲሰረዝ ካደረገ፣
- ✓ ሃብቱን ለቀድሞው ባለቤቱ እንዲመለስ ካደረገ፣
- ✓ ሃብቱ ከጠፋ ወይም ከወደመ፣
- ✓ የመብት መጠቀሚያ ጊዜው እንዲያልፍ ካደረገ፣
- ✓ ለሌላ ሰው ሃብቱን ከሰጠ ወይም እንዲሰጥ ካደረገ፣ሃብቱን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል።
- ✓ ማናቸውም ሰው ከዚህ ቀደም ያልነበረ ሃብት የሌላ ሰው ሀብት እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ ይህንን ያደረገው ሰው ሃብቱ በተፈጠረበት ጊዜ በባለቤትነቱ ስም የነበረውን ሃብት ለሁለተኛው ሰው እንዳስተላለፈ ይቆጠራል።
- ✓ ሃብት በውርስ ወይም በኑዛዜ የተላለፈ እንደሆነ ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ ሟች ሃብቱን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል።
- ✓ ሃብትን ማስተላለፍ የአንድን የንግድ ስራ ሃብት የተወሰነ ክፍል ማስተላለፍን ይጨምራል።
- ✓ አንድን ሃብት ለንብረት አጣሪ፣ በኪሳራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ ወይም ለተቀባይ (ለንብረት አስተዳዳሪ) መስጠት ሃብቱን እንደተላለፈ አያስቆጥረውም ። ስለሆነም ከዚሁ ሃብት ጋር በተያያዘ በአጣሪው፣ በባለአደራው ወይም በተቀባዩ የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ ባለቤቱ እንዳከናወናቸው ይቆጠራሉ።

3. ለሃብት የሚደረግ ወጪ

- ✓ የአንድን ሃብት ወጪ ማወቅ የሚያስፈልገው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት የሚሆነውን ወጪ ለመወሰንና ሃብቱ ሲተላለፍ የሚገኘውን ጥቅም ወይም የኪሳራ መጠን ለመወሰን እንዲቻል ነው።
- ✓ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶችን ሳይጨምር የአንድ ሀብት ወጪ የሚከተሉት ድምር ነው፦
- ✓ ሃብቱ በተገኘበት ጊዜ በዓይነት የተሰጠ ሃብት ትክክለኛ የገበያ ዋጋን ጨምሮ ባለሃብቱ ለሃብቱ የከፈለው ጠቅላላ ዋጋ፣
- ✓ ሃብቱየተገኘው በመገንባት፣ በማምረት ወይም በማልማት የሆነ እንደሆነ ለግንባታ፣ ለማምረት ወይም ለማልማት የወጣው ወጪ፣
- ✓ ሃብቱን በማግኘት ወይም በማስተላለፍ ሂደት የወጣ ማንኛውም ወጪ፣
- ✓ ሃብቱን ለመትከል፣ ለመቀየር፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት ወይም ለማሻሻል ባለሃብቱ ያወጣው ማንኛውም ወጪ።
- ✓ ግዙፋዊ ሀልወት የሌለው የንግድ ስራ ሃብት (intangible business asset) ወጪ ነው የሚባለው፦
- ✓ ሃብቱን ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ለማሻሻል ወይም ለማደስ የወጣ ወጪ እና፣ሃብቱን ለማግኘት ወይም ለማስተላፍ የወጣ ሌላ ተጓዳኝ ወጪ.ከሃብቱ ጋር በተያያዘ የወጣ ሌላ ማንኛውም ወጪ።
- ✓ በስጦታ የተገኘ ሃብት ወጪ. ሃብቱ በስጦታ በተገኘበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው።
- ✓ የአንድ ሃብት ዋጋ ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደውን ማንኛውንም ወጪ. አይጨምርም።
- ✓ የአንድ ሃብት ዋጋ የሃብቱ ባለቤት ሃብቱን የማግኘት ምርጫ እንዲኖረው ከማድረግ ጋር በተያያዘ የወጣ ወጪን ይጨምራል።
- ✓ የአንድ ሃብት ዋጋ በሃብቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በሂሳብ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን ተቀናሽ ሂሳብ አያካትትም።
- ✓ በከፊል የተላለፈ ሃብት ዋጋ ሃብቱ ሲገዛ የነበረውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ በተላለፈውና በባለሃብቱ እጅ በቀረው ሃብት ድርሻ መካከል ይከፋፈላል።

- ✓ በግብር ከፋዩ የንግድ ስራ ገቢ ውስጥ የተካተተ ካልሆነ በስተቀር ግብር ከፋዩ ሃብቱን ሲያገኝ የተቀበለው ወይም የሚቀበለው ማንኛውም ድጎማ፣ ተመላሽ፣ኮሚሽን ወይም ሌላ ማንኛውም የገንዘብ ድጋፍ በሃብቱ ዋጋ ውስጥ አይካተትም።

4. የንግድ ስራ ሃብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

- ✓ የአንድን የንግድ ስራ ሃብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ማወቅ የሚያስፈልገው፣
- ✓ ሃብቱ ሲተላለፍ የንግድ ሥራ ገቢ የሚከፈልበትን ጥቅም ወይም ተቀናሽ የሚደረግ የኪሳራ መጠን ለመወሰን
- ✓ ለሃብቱ በግብር ዓመቱ የሚፈቀደውን የእርጅና ቅናሽ መጠን ለመወሰን
- ✓ ሃብቱ ለካፒታል መዋጮ ወይም ድርጅትን መልሶ በማደራጀት ሂደት ጥቅም ላይ ሲውል የግብር ከፋዩን የካፒታል ድርሻና የድርጅቱን የካፒታል ዋጋ ለመወሰን ስለሚጠቀም ነው።
- ✓ የአንድ የንግድ ስራ ሃብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው ሃብቱን ለማግኘት ከወጣው ወጪ የሚፈቀደው የእርጅና ቅናሽ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ዋጋ ነው።
- ✓ በከፊል የተላለፈ የንግድ ሥራ ሃብት ዋጋ ነው የሚባለው በባለሃብቱ እጅ ከሚገኘው የሃብቱ ድርሻ ወጪ (ዋጋ) ላይ ለግብር ከፋዩ የሃብት ድርሻ የሚፈቀደው የእርጅና ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ዋጋ ነው።

5. ሃብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ

- ✓ ከተላለፈ ሃብት የተገኘ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ ሃብቱን ሲያስተላልፍ በዓይነት ያገኘውን ማንኛውንም ጥቅምና የገበያ ዋጋ ጨምሮ የተቀበለው ጠቅላላ ገንዘብ ነው።
- ✓ ሃብት በስጦታ የተላለፈ እንደሆነ ሃብቱ በተላፈበት ጊዜ ያለው የሃብቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ከሃብቱ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።
- ✓ አንድ ሰው ሃብቱን በማስተላለፍ ያገኘው ገቢ ሃብቱን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ከቀረበለት ምርጫ ያገኘውን ጥቅም የሚጨምር ሲሆን በዚህ ጥቅም ላይ ግብር ያልተከፈለበት ከሆነ ይህ ጥቅም ሃብቱን በማስተላለፍ ከተገኘው ገቢ ላይ ይደመራል።
- ✓ የጠፋ ወይም የወደመ ሃብት ዋጋ ለጠፋው ወይም ለወደመው ሃብት በማንኛውም መልክ ባለሀብቱ የተቀበለው ወይም የሚቀበለው ካሳ ነው።
- ✓ የንግድ ሥራ ሃብቶች በአንድ ላይ በሚሸጡበት ጊዜና የእያንዳንዱ ሃብት ዋጋ ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ ግብር ከፋዩ ሃብቶቹን በማስተላፍ የተቀበለው ጠቅላላ ዋጋ ሃብቶቹ በተላለፈበት ጊዜ ባላቸው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሰረት እንደ የድርሻቸው ይደለደላል።
- ✓ አንድ ግበር ከፋይ የተላለፈውን ሃብት ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ተክክለኛ የገበያ ዋጋ የሃብቱ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

6. ጥቅምን ወይም ኪሳራን ስለማስተላለፍ

- ✓ በሚከተለው ሁኔታ ሃብት ሲተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ወይም ኪሳራ ለግብር አከፋፈል (አወሳሰን) ከግምት ውስጥ አይገባም።
- ✓ ባልና ሚስት ሲፋቱ በንብረት ክፍፍል ወደየተጋቢዎች ሃብት ሲተላለፍ።
- ✓ የባለሃብቱን መሞት ተከትሎ ሃብቱ ለውርስ አጣሪው ወይም ለወራሹ ሲተላለፍ።
- ✓ ለጠፋ ወይም ለወደመ ሃብት በተከፈለ ካሳ ሃብቱ በጠፋ ወይምበወደመበአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ባለስልጣኑ በሚፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ሃብት የተተካ እንደሆነ።

- ✓ የጠፋው ወይም የወደመው ሃብት ዋጋ የሚቀንስ የሆነ እንደሆነ ባለሃብቱ ሃብቱ በጠፋ ወይም በወደመ በስድስት ወር ወይም ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ በረዘመ ጊዜውስጥ ለመተኪያ በተሰጠው ገንዘብ /ካሳ/ ዋጋው የሚቀንስ ለንግድ ስራ የሚውል ተመሳሳይ ሃብት ያፈራ ወይም የተካ እንደሆነ።
- ✓ የትዳር መፍረስን ተከትሎ በሚፈጸም የንብረትና የሃብት ክፍፍል ምክንያት ሃብት ለሚስት ወይም ለባል ሲተላለፍ ወይም የባለሃብቱን መሞት ተከትሎ የሚች ሃብት ለውርስ አጣሪ ወይም ለወራሽ በሚተላፍበት ጊዜ ሃብቱ የተላለፈለት ሰው ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ ለሀብቱ በወጣው ወጪ ልክ ሃብቱን እንዳገኘው ይቆጠራል።
- ✓ በጠፋው ወይም በወደመው ሃብት ምትክ የተተካው የመተኪያ ሃብት ዋጋ ከተተካው ሃብት ዋጋ የበለጠ እንደሆነ የመተኪያውሃብት ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከተተኪው ሃብት ዋጋ ላይ በብልጫ የታየው ገንዘበ መጠን ተጨምሮበት ነው።
- ✓ ለተተካው ሃብት የተከፈለው ዋጋ ከመተኪያ ሃብት ዋጋ የሚበልጥ ከሆነ የመተኪያው ሃብት ዋጋ ነው የሚባለው ሃብቱ በተላለፈበት ጊዜ ባለው በተተኪው ሃብት ዋጋ ላይ በብልጫ ለተተኪው ሃብት የተከፈለው የገንዘብ መጠን ተቀንሶ ነው። ነገር ግን ከዜሮ በታች መሆን የለበትም።
- ✓ ለተተካ ሃብት የተከፈለው ዋጋ ከመተኪያው ሃብት ዋጋ የበለጠ እንደሆነ ከተተኪው ሃብት ከተከፈለው ገንዘብ ላይ የመተኪያውን ሃብት ዋጋ በመቀነስ የሚገኘው ልዩነት በግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ መካተት አለበት።

7. የተላለፉ ሃብቶችን ስለመመዝገብ

የአንድን ሃብት መተላለፍ ለመቀበል፣ ለመመዝገብ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ መተላለፍን ለማጽደቅ በህግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሰው በሃብቱ መተላለፍ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሰረት መክፈል የሚገባው ማንኛውም ግብር መክፈሉን ሳይረጋገጥ ሃብቱ መተላለፉን ሊቀበል፣ ሊመዘግብ ወይም ሊያጸድቅ አይችልም።

8. የተመለሰ ወጪ

ግብር ከፋዩ አስቀድሞ ተቀናሽ የተደረገውን ወጪ ወይም የተሰረዘ የማይሰበሰብ ዕዳ የሚያካክስ የገንዘብ መጠን መልሶ የተቀበለ እንደሆነ ገንዘቡን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ገቢ ተቆጥሮ ተቀናሽ ተደርጎለት ከነበረው ገቢ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ምድብ እንደ ገቢ ይያዛል።

9. በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን

በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን ወይም የተፈጸመ ክፍያ ዋጋ የገንዘቡ መጠን በተገኘበት ወይም ክፍያው በተፈጸመበት ጊዜ ሃብቱ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሲሆን ፣ ዋጋው ሲወሰን ሃብቱን በማስተላለፍ መብት ላይ የተጣለው ገደብ ከግምት ውስጥ አይገባም።

ሃብቱ በባንክ ወይም በግብር ዕዳ ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን ዕዳ የተያዘና እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት መሆኑ ዋጋውን አይቀንሰውም።

10. ወጪዎችን ስለማከፋፈል

ማንኛውም ወጪ፣

- ✓ ከአንድ በላይ የሆኑ የገቢ ዓይነቶችን ለማግኘት የወጣ ከሆነ ወይም፣
- ✓ አንድን የገቢ ዓይነት ለማግኘትና ለሌሎች ዓላማዎች የዋለ ከሆነ
- ✓ የስራውንና የወጪዎቹን ባህሪና መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ወጪው ይከፋፈላል።

11. የገንዘብ ምንዛሬ

- ✓ ግብር ከፋዮች በወጭ ምንዛሪ የተፈጸመ ክፍያ ወይም የተደረገ ግብይት ሲኖራቸው የገንዘቡን መጠን (ወጪም ሆነ ገቢ) በብር መግለጽ አለባቸው።
- ✓ የገንዘቡ መጠን በውጭ ምንዛሪ የተያዘ ከሆነ ገንዘቡ በሂሳብ መዝገብ በሚመዘገብበት ጊዜ ባለው የብሄራዊ ባንክ የምንዛሬ ተመን ተሰልቶ ወደ ብር መለወጥ አለበት።
- ✓ በውጭ ምንዛሬ ግብይት የደረሰ ኪሳራ ወይም የተገኘ ጥቅም የሚሰላበትን ዘዴና የውጭ አገር ገንዘብ ወደብር የሚቀየርበትን ሁኔታ የሚወሰን መመሪያ ባለስልጣኑ ያወጣል።

5.5.1. ከግብር ለመሸሸ የሚደረገውን ጥረት ስለመከላከል

i. ገቢን መከፋፈል

- ✓ ግብር ከፋዩ ግብር ለመቀነስ ሲባል ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በሚኖረው ግብይት ያገኘውን ገቢ ለመከፋፈል የሞከረ እንደሆነ ባለስልጣኑ የሁለቱንም ሰዎች ገቢዎች እና ተቀናሽ ወጪዎች አስተካክሎ ሊወሰን ይችላል።
- ✓ ግብር ለመከፋፈል ተሞክሯል የሚባለው፣
- ✓ ግብር ከፋዩ ገቢውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍና ገንዘቡ ወይም ሃብቱ የተላለፈለት ሰው ከተላለፈው ሃብት ወይም ገንዘብ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ ወይም
- ✓ ሃብቱ ወይም ጥሬ ገንዘቡ የተላለፈበት ምክንያት የአስተላለፈውን ወይም የተላለፈለትን ሰው ገቢ ዝቅ ለማድረግ ወይም ወጪውን ለማናር የሆነ እንደሆ ነው።
- ✓ ገቢን ለመከፋፈል የተሞከረ መሆኑን ለማረጋገጥ ለተላለፈው ሃብት የተሰጠውን ዋጋ ባለስልጣኑ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

ii. ስለ ማሸጋገሪያ ዋጋ

- ✓ በገበያ ዋጋ መርህ ያልተደረገ ማንኛውም ግብይት ሲኖር ባለስልጣኑ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ከግብይቱ ጋር በተያያዘ የሚገኘውን ትክክልኛ ገቢ ፣ጥቅም፣ ተቀናሽ ኪሳራ ወይም ማካካሻ ግብይቱን ባደረጉት ወገኖች መካከል ሊያከፋፍል ወይም ሊደለድል ይችላል።
- ✓ አንደኛው ተዋዋይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ሆኖ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆንና ሌላኛው ተዋዋይ ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖር በሚሆንበት ጊዜ ማንኛም የገቢ፣ የወጪ፣ የተቀናሽ ሂሳብ፣ የኪሳራ ወይም የግብር ማካካሻ ክፍፍልና ድልድል የሚደረገው ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል።
- ✓ መመሪያው፡-
- ✓ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት የገቢ ወይም የወጪ ድልድል በሚያደርግበት ሁኔታ ላይ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ ላለው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት የገቢ ወይም የወጪ ድልድል በሚያደርግበት ሁኔታ ላይ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወኑ ግብይቶችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
- ✓ በዋናነት የማሸጋገሪያ ዋጋን በማጋነን ወይም በማሳነስ ታክስ የማጭበርበር ተግባር የሚፈጸመው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች በሚደረግ ግብይት ነው።

- ✓ በገበያ ዋጋ መሰረት የሚደረግ ግብይት የሚባለው ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች በገበያ መርህና ዋጋ መሰረት የሚያደርጉት ግብይት ነው።
- ✓ የተዋዋዮቹ ጥቅሞች አንዱ ለሌላው የማይገዛና እርስ በርስ ተወዳዳሪዎች (independent and competitive interests) መሆን አለባቸው።

iii. ከግብር ለመሸሽ የሚደረጉ ዕቅዶች

- ➢ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች ከግብር ለመሸሽ የሚያስችል ዕቅድ በማዘጋጀትና በመተግበር የግብር ጥቅም ያገኙ እንደሆነ ባለስልጣኑ፣
  - ✓ ይህ የተደረገበት ብቸኛ ወይም ዋነኛ ዓላማ የግብር ጥቅም ለማግኘት መሆኑን በማረጋገጥ፣
  - ✓ ዕቅዱ ወይም ስምምነቱ እንዳልተደረገ ወይም እንዳልተተገበረ በመቁጠርና አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበትን ሰው ወይም ከዕቅዱ ጋር ግንኙነት ያለውን ሌላ ሰው ግብር ሊወሰን ይችላል።
  - ✓ ለግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያም ይሰጣል።
  - ✓ "ዕቅድ" የሚለው ቃል ስምምነቱ ህጋዊ ቢሆንም ባይሆንም ወይም በጽሁፍ ወይም በሁኔታ የተደረገ ቢሆንም ስምምነትን፣ ማመቻቸትን ቃል ኪዳን መግባትን፣ ሃሳብ ማቅረብንና መፈጸምን ያጠቃልላል።
- ➢ "የግብር ጥቅም" የሚለው ቃል ደግሞ፣
  - ✓ ሊከፈል የሚገባን ግብር ማስቀረትን ወይም መቀነስን፣
  - ✓ ግብር የመክፈል ኃላፊነትን ማዘግየትን
  - ✓ ከግብር በመሸሽ የሚገኝን ማንኛውንም ጥቅም ይጨምራል።
  - ✓ ከግብር ለመሸሽ ከሚደረጉ ዕቅዶች ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው "tax planning" ነው።
  - ✓ ከግብር መሸሽ (tax avoidance) ግብር ከመሰወር (tax evasion) የሚለይ ሲሆን የመጀመሪያው የህግ ከፍተቶችንና የፖሊሲ ቀዳዳዎችን በመጠቀም ህጉ ተፈጻሚ እንዳይሆንባቸው ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ጋር የተያያዘ ሆኖ ጥፋቱ በአስተዳደር የሚያስቀጣ ነው። ሁለተኛው ግን ግብር ላለመክፈል በማሰብ ሆነ ብሎ ህግን በመጣስና ህጋዊ ግዴታን ባለመወጣት መክፈል የሚገባን ግብር በከፊል ወይም በሙሉ አለመክፈል ወይም አነስተኛ ግብር ለመክፈል ገቢና መረጃን መደበቅን ያጠቃልላል።

5.5.2. የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ

- ❑ ***የንግድ ስራ ማቋረጥማለት*** *በታክስ ከፋይነት ተመዝግቦ የንግድ ሥራ ሲሰራ የነበረና የንግድ ሥራውን ማቆሙን በፅሁፍ ለታክስ ባለስልጣኑ በማስታወቅ ከታክስ ከፋይነት የተሰረዘ ነው።*

➢ *ይህ ሕግ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ባገኘ ታክስ ከፋይ ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል።*

➢ *ማንኛውም ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራ ካቋረጠ በኋላ ገቢ ሊያገኝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው።*

- ✓ *ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራውን ካቋረጠ በኋላ* ***የካፒታል አቃዎችን ጨምሮ በአጁ የሚገኙትን ያልተሸጡ አቃዎች በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ፣***
- ✓ *በንግድ እንቅስቃሴ ወቅት* ***ሊሰበሰብ የማይችል ገቢ ነው ተብሎ የተሰረዘ ገቢ*** *የንግድ ሥራው ከተቋረጠ በኋላ ሲሰበሰብ፣*

- ***የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚወሰነው ግብር***

  ሀ) ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ የሚሸጣቸው እቃዎች የተሸጡበትን ዋጋ ማረጋገጥ የማይቻል ከሆነ እቃው ***የተገዛበት ዋጋ ወደ ሽያጭ ተቀይሮ*** *ግብሩ ይወሰናል።*

  ለ) ታክስ ከፋዩ እቃውን የሸጠው የሒሳብ መዝገብ ለሚይዝ ታክስ ከፋይ ከሆነ እቃው የተሸጠበት ዋጋ ገዢው በሚያዘጋጀው ***የግዥ ማረጋገጫ ሰነድ*** (Purchase Voucher) ***መሰረት ይወሰናል።***

  ሐ) ታክስ ከፋዩ ***ድርጅቱን ሲዘጋ በእጁ ያሉትን እቃዎች ቆጥሮለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።***

  መ) ታክስ ከፋዩ ድርጅቱን ከዘጋ በኋላ በሸጣቸው እቃዎቹ ***የመዝገብ ዋጋ*** (Book Value) ***ከተሸጠበት ዋጋ ላይ ተቀንሶ በሚገኘው ልዩነት ላይ የሚሰላ ይሆናል።***

  - ✓ ***የንግድ ትርፍ ግብርየመክፈል ግዴታ አለበት።***
  - ✓ *የንግድ ስራ ገቢ ተፈጻሚ የሚደረገው የትርፍ ህዳግ ግብር* ***ለደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች ጥቅም ላይ የሚውለው የትርፍ ህዳግ ይሆናል።***

የመከራ ጥያቄ ሰባት

2 ኛ. የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዴት ነው የሚወሰነው?

3 ኛ.ከግብር መሸሽ (tax avoidance) እና ግብር መሰወር (tax evasion) መካከል ያለውን ልዩነት አብራ

ማጠቃለያ

ግብር የመዝገበ ቃላት ፍችው ሲታይ መንግስት በህግና ደንብ ላይ ተመስርቶ ከህዝብና ከድርጅቶች ገንዘብ የሚያገኝበት መሳሪያ ነው።ዜጎች በመነገድ ንብረት በማከራየት፣ዕውቀታቸውን በመሸጥ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ከሚያገኙት ገቢ ላይ ህግ በተቀመጠው መሰረት ግብር መክፈል ይጠበቅባቸዋል።ስለዚህ ግብር ህብረተሰቡ ወይም ግብር ከፋዮች ለመንግስት በግዴታ ክፍያ የሚፈጽሙበት መንገድ/ስርአት ሲሆን በአንጻሩ ግን መንግስት ለሕ/ሰቡ በለውጡ ወይም በምትኩ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ልዩነት ሳይፈጥር ለሚያቀርበው አገልግሎትና መሰረተ ልማቶች የሚያውለው ገንዘብ ነው።

የግብር/ታክስአስፈላጊነት /ጥቅም

ግብር ከእያንዳንዱ ግለሰብ የየእለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሲሆን ጠቀሜታዎቹም አያሌና ዘርፈብዙ ናቸው።የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ግብር ለኢኮኖሚ ልማት፣ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ለባህል እድገት፣ለሀገር ደህንነት፣ለፍትህና መልካም አስተዳደር መስፈን፣ለአከባቢጥበቃ፣ሀገርን ከጠላት ለመከላከል፣ዜጎችበሰላም ወጥተው በሰላም ሰርተውና ውለው ለመግባት፣ደህንነታቸውና ሰላማቸውን ለመጠበቅ፣ትምህርት ቤቶች፣ሆስፒታሎች፣መንገዶች፣የህይል አቅርቦቶችን ለመስፋፋት፣ኢኮኖሚን ለመነቃቃት፣ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ልማትን ለማፋጠን፣የሕ/ሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ኢኮኖሚን ለማረጋጋት፣በዜጎች መካከል ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ እና የመሳሰሉት ስራዎችን ለማከናወን የሚውል ገንዘብ ነው።

ስለሆነም ሁሉም ግብር ከፋይ የግብር አስፈላጊነትን ጠንቅቆ በመረዳት ከሚያገኘው ገቢ ላይ የግብር ህጉ በሚፈቅደው መሰረት መክፈል ይኖርበታል።

ማጣቀሻ (Referance)

ገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 979/2008

ገቢ ግብር ማሸሻያ አዋጅ ቁ. 1395/2017

የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008

የገቢ ግብር ደንብ ቁ. 410/2009

የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁ. 410/2009

መመሪያ ቁ. 138/2010 ታክስ በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ የወጣ *መመሪያ*

መመሪያ ቁ. 176/2014 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ *መመሪያ*

መመሪያ ቁ. 1/2011 ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈፃጸም *መመሪያ* (የገንዘብ ሚኒስቴር)

መመሪያ ቁ. 5/2011 ስለ ተቀናሽ ወጪዎች የወጣ *መመሪያ* (የገንዘብ ሚኒስቴር)

መመሪያ ቁ. 8/2011 የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም (ገንዘብ ሚኒስቴር)

መመሪያ ቁጥር 146/2011146-2011 የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በተገኘ ገቢ ላይ ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ *መመሪያ*